# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 210 መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# የ2016 ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከግንቦት 1 እስከ ግንቦት 5 ይካሄዳል

## - ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት እንደሚፈጸም ይጠበቃል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የ2016 ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ እና ባዛር ከግንቦት 1 እስከ ግንቦት 5 እንደሚካሄድ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በኤክስፖው ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት እንደሚፈጸም ይጠበቃል፡፡

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት አስተባባሪ አያና ዘውዴ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ለማሳደግ እየተሠራ ሲሆን የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከግንቦት 1 እስከ ግንቦት 5 2016 ዓ.ም ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

የኤክስፖው ዋንኛ ዓላማ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የተመረቱ ምርቶችና ቴክኖሎጂዎችን በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ፣ አዳዲስ የውጪ ቴክኖሎጂዎችንና

የ2016 ኢትዮጵያ ታምርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢትዮጵያና ታንዛኒያ የአቪዬሽን ግንኙነት እየጠነከረ መጥቷል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና ታንዛኒያ የአቪዬሽን ግንኙነት ከበረራ ባሻገር በቴክኒክና ሥልጠና መስኮች እየጠነከረ መምጣቱን በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሽብሩ ማሞ አስታወቁ፡፡

በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሽብሩ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከታንዛኒያ ጋር ያላት የአቪዬሽን ስምምነት የበረራ ብቻ ሳይሆን የቴክኒክና ሥልጠና ዘርፎችንም ያካተተ ነው።

እ.አ.አ. ከ2016 እስከ 2023 ባሉ ጊዜያት ውስጥ ብቻ ከ75 በላይ ፓይለቶችና ከ25 በላይ የታንዛኒያ ኢንጂነሮች በዘርፉ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጠናዎችን ወስደዋል ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በታንዛኒያ ያደረጉት ጉብኝት በሁለቱ ሀገራት መካከል በአቪዬሽን መስክ ያሉ ስምምነቶችን በቴክኖሎጂና በተሞክሮ ልውውጦች የበለጠ የሚያጎለብት ነው፤ ለስምምነቱ ተግባራዊነት የኢትዮጵያ መንግሥት በትኩረት እየሠራበት ነው ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያና ታንዛኒያ በአቪዬሽን መስክ ያላቸው ግንኙነት ረጅም ጊዜን ያስቆጠረና ጠንካራ ሲሆን የአሁኑ ግንኙነት ደግሞ የበለጠ የመጠናከር እድል ያለው ዘርፍ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሁለቱ ሀገራት መካከል በአቪዬሽን መስክ ከ1966 ጀምሮ የተፈረሙ የመግባቢያ ስምምነቶች አሉ። በአሁኑ ጊዜ ስምምነቶች እየታደሱ፣ እየተከለሱና እየሰፉ ነው፡፡

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ ቀዳሚው የአየር መንገድ ሲሆን የበራራ መዳረሻዎችን ማስፋት ብቻ ሳይሆን በጥገናና በሥልጠና መስክም ራሱን

የኢትዮጵያና ታንዛኒያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር ሽብሩ ማሞ






# የኅብረተሰቡ

## የጤና አለኝታዎች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

በጤናው ዘርፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በመስጠት ጤናማ ትውልድን ለመፍጠር የሕክምና ተቋማትን ከማስፋፋት ጀምሮ ሰፊ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡

የኅብረተሰቡ የጤና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የብርዕ፣ የአገዳና የጥራጥሬ ሰብሎችን ምርታማነት ለማሳደግ የምርምር ሥራ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በብርዕ፣ በአገዳና በጥራጥሬ ሰብሎች ላይ አዳዲስ ዝርያዎችን በማፍለቅ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግና ምርታማነትን ለማሳደግ የምርምር ሥራዎች

የብርዕ፡ የአገዳና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በቅጡ መረዳትን የሚሻው “ዳውን ሲንድረም”

**ማሕሴት ብዙነህ**

የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ወይም ዳውን ሲንድረም በተፈጥሯዊ ስህተት 21ኛ ዘረ-መል በሚደገምበት ጊዜ የሚፈጠር የተፈጥሮ ክስተት ነው፡፡ ይህም በመደበኛ ሁኔታ ካለው 46 ዘረ-መል በተለየ ሁኔታ ከዳውን ሲንድረም ጋር የሚወለዱ ሕፃናት 47 ዘረ-መል እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ዓለም አቀፍ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሚወለዱ 10 ሺህ ሕጻናት ውስጥ ከ10 እስከ 16 የሚሆኑት ሕጻናት ከዳውን ሲንድረም ጋር የመወለድ ዕድል አላቸው። በኢትዮጵያ ውስጥም ከ5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይገመታል፡፡

በሀገራችን ውስጥ ያሉት የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች አይችሉም የሚል ፍርጃ፣ ከፍተኛ አድሎ እና መገለል የሚደርስባቸው ከመሆኑ በተጨማሪም የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለበት ልጅ መውለድ የሚያሸማቅቅ እና እንደ እርግማን የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡

ታዲያ ይህንን የግንዛቤ እጥረት ለመፍታትና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በሀገራችን በዳውን ሲንድረም ዙሪያ የሚሠሩ ማኅበራትና ግለሰቦች ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በየዓመቱ ይህ መጋቢት ወር የዳውን ሲንድረም ወር በመባል ይታወሳል፡፡

የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ላይ ትኩረቱን ያደረገው የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ብሔራዊ ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ የሸዋጌጥ ክብረት እንደሚሉት፤ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ወይም ዳውን ሲንድረም ያለባቸው ልጆች በማኅበረሰቡ ዘንድ አይችሉም የሚል የተሳሳተ እሳቤ ምክንያት የተለያዩ አድሎ እና መገለል ይደርስባቸዋል፡፡

በተለይም ዳውን ሲንድረምን በአግባቡ ባለመረዳት ከኦቲዝም ጋር የማመሳሰል ሁኔታ ያለ ሲሆን ባላቸው የተለየ ተፈጥሮ ምክንያት እንደእርግማንና የፈጣሪ ቁጣ የመቁጠር አሉታዊ አስተሳሰብ አለ ይላሉ፡፡ በዚህም ልጆቹ ትምህርት ቤት አይሄዱም፤ ብሎም እንደ ልደት እና መሰል ፕሮግራም ላይ አይጠሩም፡፡

በዚህ ወር በስፋት የሚከበረው የዳውን ሲንድረም በዓልም ዓላማው የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው




ሰዎች ተወዳዳሪ የሥራ አቅም እንዳላቸውና ሕይወታቸውን ያለጥገኝነት መምራት እንደሚችሉ ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ መሆኑን ነው ወይዘሮ የሸዋጌጥ የሚናገሩት፡፡

የዘንድሮ የዳውን ሲንድረም በዓልም “ፍረጃ ይቁም” በሚል መሪ ቃል ዳውን ሲንድረም ያለባቸው ልጆች አይችሉም በሚል የሚፈርጀውን ያቁም የሚል ትልቅ መልዕክት በመያዝ ይከበራል፡፡

በመሆኑም ለኅብረተሰቡ ትክክለኛውን ግንዛቤ በመፍጠር ዳውን ሲንድረም ያለባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች መብት ማስከበርና በማናቸውም መስኮች ማካተት እንዲቻል መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ የሸዋጌጥ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ከተደበቁበት በማውጣት ወደ ኅብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ፣ ድጋፍና እንክብካቤ በመስጠት፣ የሚደርስባቸውን አድሎ እና መገለል በማስቀረት እኩል ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባልም ባይ ናቸው፡፡

መንግሥትም አካታች የሆነ ፖሊሲና ሕጎችን በማዘጋጀት እና በመቆጣጠር እኩል የሆነ ትምህርት፣ የሥራ ዕድልና ሀገራዊ ተሳትፎ እንዲሁም ጥቃት እንዳይደርስባቸው መከላከል እንደሚገባም ሥራ አስኪያጇ አስታውቀዋል፡፡

ከ28 ዓመታት በላይ ያስቆጠረው ማኅበሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ በውስጡ አጠቃላይ 15 ሺህ በላይ አባላቶች አሉት፡፡ ማንኛውም ዳውን ሲንድረም ያለበት ሰው በቤት ውስጥ ተደብቆ ከመቀመጥ ወደ ማኅበሩ መቀላቀል ይችላል፡፡ ለዚህም ሁሉም ኃላፊነት በመውሰድ መርዳት አለበትም ብለዋል፡፡

ሌላው በሀገራችን ከሚገኙ በዳውን ሲንድረም ዘርፍ የተሰማሩ ማኅበራት ውስጥ አንዱ ዲቦራ ፋውንዴሽን ነው፡፡ ዲቦራ ፋውንዴሽን በ2011 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን የአዕምሮ ውስንነት ያለባቸው ሕጻናት መንከባከቢያ ማዕከል ነው፡፡

ማዕከሉ አሁን ላይ 1900 ዳውን ሲንድረም ያለባቸው ሕጻናትና ጎልማሳ አባላት እንዳሉት የሚናገረው የማኅበሩ የፈንድ ሬዚንግ እና ምርምር ባለሙያ ዮሐንስ ግዛው(ዶ/ር)፤ ማኅበሩ ዳውን ሲንድረም ያለባቸውን ዜጎች በትምህርት እና ጤና ዘርፍ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እየሰጠ እንደሚገኝ ያናገራሉ፡፡

በዳውን ሲንድረም የተጠቃ ሰው ትርፍ ወይም ተጨማሪ የዘረ መል ቅንጣት ይኖራቸዋል። ይህም ችግር ያለባቸውን ግለሰቦች ከሌለባቸው ሰዎች የተለዩ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ሲሉም ያብራራሉ።

ዮሐንስ (ዶ/ር)እንደሚሉትም፤ ከተለመደው የተለየ የጭንቅላትና የፊት ቅርጽ፣ አንገት አካባቢ ድርብርብ ቆዳ፣ ልል የሰውነት ጡንቻ፣ ቀጥ ያለና ወጥ የሆነ የመዳፍ መስመር፣ ያንገት ማጠር፣ ትንሽ ወይም ያልተለመደ የጆሮ ቅርፅ፣ አጭር እና ሰፊ የእጅ መዳፎች የመሳሰሉት አካላዊ ምልክቶች ይታዩባቸዋል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ የእይታ፣ የደም፣ የሥርዓተ-ልመት፣ የመተንፈሻ አካል እና ከ40-65 በመቶ የሚሆኑት የልብ ክፍተት የመሳሰሉት ከቀላል እስከ ከባድ ተጓዳኝ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እነዚህ ተጓዳኝ የጤና ችግሮችም በሕክምና ሊድኑ እንደሚችሉ ያብራራሉ::

ቀኑ መከበሩ ግንዛቤ መፍጠር እንደሌሎች ሕጻናት ትርጉም ባለው ሁኔታ ከማኅበረሰቡ ጋር አንድ ላይ በመሆን ማሳካት የሚችሉበትን ሁኔታ ማካተት፤ ሌሎች ልጆች ሊደርሱበት የሚችሉበትን ደረጃ መድረስ እንደሚችሉ በማሳወቅ ያለውን አሉታዊ እሳቤ መቀየር ይገባል ይላሉ፡፡

ዳውን ሲንድረም ያለባቸው ሰዎች በትኩረት ከተሠራባቸው እንደማንኛውም ዜጋ መሥራት፣ መማር፣ ለራሳቸው ብሎም ለሕዝብ መሥራት እና መጥቀም የሚችሉ በመሆኑ ሁሉም የኅብረተሰብ አካል ኃላፊነቱም መወጣት አለበት ብለዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲውና ሁዋዌ ያደረጉት ስምምነት በቴክኖሎጂው ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ያግዛል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ሕዋዌ ቴክኖሎጂስ የተፈራረሙት ስምምነት በቴክኖሎጂው ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት እንደሚያግዝ ተገለጸ፡፡

በመድረኩ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ቢቂላ ተክሉ(ዶ/ር) እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያው ራስ ገዝ የከፍተኛ ተቋም በመሆን አዲስ ጉዞ ጀምሯል፡፡ በዚህም የአምስት ዓመታት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

በዚህ ስትራቴጂክ እቅድ ሁዋዌን ከመሳሰሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መሥራት አንዱ የትኩረት አቅጣጫው መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ለተማሪዎች ትልቅ የአቅም ማጎልበቻ መንገድ በመሆን ብቁ ምሩቃንን ወደ ገበያ ለማውጣት ያግዛል ብለዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ዩኒቨርሲቲው ከ"ሁዋዌ ቴክኖሎጂስ ኢትዮጵያ" ጋር በትብብር ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ በዚህም በርካታ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና ምሩቃን የሥልጠናና የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል፡፡

የተፈረመው ትብብርም የሁለቱን ተቋማት አጋርነት ወደላቀ ደረጃ የሚያሳድግ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ከሁለቱ ተቋማት ባለፈ ለቴሌኮም ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ነው ብለዋል፡፡

የሁዋዌ ቴክኖሎጂስ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሊዮ ጂፋን በበኩላቸው፤ ተቋሙ ባለፉት ዓመታት አብሮ ሲሠራ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን ለማድረግና ዘርፉ ሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍ ያለድርሻ እንዲኖረው የሰጠውን ትኩረት አድንቀው፣ ሁዋዌ ቴክኖሎጂስ ኢትዮጵያ ለዲጂታል ኢትዮጵያ እውን መሆን የድርሻውን ለማበርከት እየሠራ ነው፤ ተማሪዎች የነገ ፈጣሪዎችና መሪዎች ናቸው ብለዋል፡፡

በመሆኑም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር አቅማቸውን የሚያጎለብቱበትንና ተሰጥዖዋቸውን አውጥተው ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን እድል ለመፍጠር ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ከአንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በቅርበት በመሥራት ለተማሪዎች የሥራ ላይ ልምምድና ሌሎችንም ዕድሎች በመፍጠር ዘርፉን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት እንደሚያግዝ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ሕዋዌ ቴክኖሎጂስ ኢትዮጵያ በጋራ ለመሥራት ሰሞኑን የተፈራረሙት የመግባቢያ ስምምነት በቴሌኮም ቴክኖሎጂ ዘርፍ ገበያው የሚፈልገውን ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ተጠቁሟል፡፡

በተጨማሪም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪዎች በሁዋዌ የሥራ እድል ማግኘት የሚያስችል ዓውደ ርዕይ ተካሂዷል፡፡

# ጠንካራ የሚዲያ ገጽታ ለመገንባትና የባለሙያዎችን ብቃት ለማሳደግ ሰፊ ጥረት ሊደረግ ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ :- መገናኛ ብዙኃን ጠንካራ የመረጃ ምሕዳር እንዲፈጥሩ እና ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ መንግሥት እና የሚመለከታቸው አካላት ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ሲል የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ጥሪ አቀረበ።

የምክር ቤቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አቶ ታምራት ኃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ነፃ እና ጠንካራ መገናኛ ብዙኃን ለመፍጠር በመገናኛ ብዙኃን መካከል ያለው ትብብር እና የጋዜጠኞችን አቅም ማሳደግ ዋነኛው ሥራ ሊሆን ይገባል።

ምክር ቤቱ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በመሆን አባላቱን ወደ 82 ማሳደግ መቻሉን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ታምራት ገለጻ፤ ምክር ቤቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከፀጥታ ጋር በተገናኘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማስተካከል የግጭት አፈታት ዘገባና የሠላም ጋዜጠኝነትን እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በርከት ላሉ ጋዜጠኞች በየጊዜው ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል ።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ ማንኛውም በሃገሪቱ የሚወጡ ዜናዎችን እና ሌሎች ጽሑፎችን የሚገመግሙ እና ክትትል የሚያደርጉ ክፍሎችን ለማቋቋም እየሠራ መሆን አንስተው ዘገባዎቹን ለማረጋገጥ እና የሚጋሩበትን መንገድ ለመከታተልም የዲጂታል የሚዲያ ሥነ ምግባር ደንቦችን ተግባራዊ አድርጓል ሲሉ ገልጸዋል ።

የማኅበረሰቡን ሃሳብ ለማንጸባረቅና ለመደገፍ እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ ምክር ቤት ከሃገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ስምምነት



**አቶ ታምራት ኃይሉ**

ለመፈራረም በሂደት ላይ መሆኑን የተናገሩት አቶ ታምራት በቀጣይ ዓመትም ከመላው ሀገሪቱ ለተውጣጡ ከአንድ ሺህ 900 በላይ ጋዜጠኞች ሥልጠናዎችን ለመስጠት ማቀዱን ጠቁመዋል ።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የምሥራቅ አፍሪካ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት አባል ለመሆን መዘጋጀቱን ገልጸው ይህም የመረጃ ልውውጥን ለማቀላጠፍ እና የፕሬስ ነፃነትን ለማስቀጠል ትልቅ ሚና እንዳለው አስታውቀዋል።

አክለውም ምክር ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ሰፊ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ መሆኑን ገልጸው የመገናኛ ብዙኃን የእርስ በእርስ ቁጥጥር ሥርዓትን በመዘርጋት የመገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኞች ከዘገባቸው ጋር ተያይዞ ከተለያዩ አካላት የሚደርስባቸውን ጫና በመቀነስ በከፍተኛ ኃላፊነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማስቻል ዋነኛ ተግባሩ መሆኑን አስታውሰዋል።


ረዳት ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ

# በድሬዳዋ የሕግ ታራሚዎች የበደሉትን ማኅበረሰብ ለመካስ እየሠሩ ነው

**ተስፋ ፈሩ**

ድሬዳዋ፡- በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት የሚገኙ የሕግ ታራሚዎች የበደሉትን ማኅበረሰብ የሚክሱበት ዕድል እንዳገኙ ተገለፀ።

የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ዳይሬክተር ረዳት ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በስድስት ማኅበራት የተደራጁ ታራሚዎች የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ በማቅረብ የበደሉትን ማኅበረሰብ የሚክሱበት ዕድል አግኝተዋል።

በታራሚዎቹ የሚመረቱት ብሎኬት፣ ፊሳሽ ሳሙና፣ የኤሌክትሪክ ምድጃ፣ የፍራፍሬ ጭማቂ እና የባሕል አልባሳት ከድሬዳዋ አልፈው ጅግጅጋ እና ጭሮ ድረስ እየተላኩ እንደሚገኙም ገልፀዋል።

በሳንቡሳ ምርት ተደራጅተው በ6ሺ ብር ካፒታል ሥራ የጀመሩ ታራሚዎች 200 ሺ ብር እንዲሁም ፈሳሽ ሳሙና አምራች ታራሚዎች ከ35 ሺ ብር ካፒታል ተነስተው 300 ሺ ብር ማስመዘገባቸውን ጠቁመው፣ "ይሄን የምናደርገው ታራሚዎች የበደሉትን ማኅበረሰብ እንዲክሱ እና ገቢ አግኝተው ከማረሚያ ቤት በሚወጡበት ጊዜ በተማሩበትና በሠለጠኑበት ሙያ የራሳቸውን ሥራ መጀምር እንዲችሉ ነው" ብለዋል፡፡

በማረሚያ ቤቱ ከሚገኙት ታራሚዎች ከፊሉ በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ ተሠማርተው እንደሚውሉ ጠቁመው፣ ታራሚዎች ምርታቸውን በቀጥታ ለኅብረተሰቡ ማድረስ እንዲችሉ የመሸጫ ቦታ ሼድ ቢመቻችላቸው ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ ነው ያሉት።

ማረሚያ ቤቱ እየሠራ ያለው ሥራ ታራሚዎች ወደ ማኅበረሰቡ ሲቀላቀሉ የሰው እጅ እንዳያዩ ከማድረግ ባለፈ፣ ሰው ከሠራ ሀብት ማፍራት ይችላል የሚል እምነት እንዲይዙና በአቋራጭ ለመክበር ከሚደረግ ሕገወጥ እንቅስቃሴ እንዲቆጠቡ የሚያደርግ ነው ያሉት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ ብዙዎች ከማረሚያ ቤቱ ወጥተው የራሳቸውን ፀጉር ቤት እንዲሁም ፈሳሽ ሳሙና እና ብሎኬት ማምረቻ እንደከፈቱ ተናግረዋል።

አርዓያነት ላላቸው ታራሚዎች በቀጣዩ 2017 ዓ.ም. መንጃ ፈቃድ ማስተማር ለመጀመር መታቀዱን ያነሱት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ ማረሚያ ቤቱን የኢንዱስትሪ ማዕከል የማድረግ ሕልም አለን። ለዚህም ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፣ ከከተማዋ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ እና ከኢትዮ ጣሊያን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመን በትብብር እየሠራን እንገኛለን ብለዋል።

በማረሚያ ቤቱ የሚገኘው ሰፊ የሰው ጉልበት ወደ ምርት መቀየር አለበት የሚል እሳቤ ይዘን እየተንቀሳቀስን ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ከሀረማያ ዩኒቨርስቲ ጋር በከተማ ግብርና ላይ በጋራ ለመሥራት በሂደት ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ከማረሚያ ቤታችን የሚወጡ ታራሚዎች በሥነምግባራቸው አንቱ የሚባሉ ባለሙያዎች እንዲሆኑ ስለምንፈልግ በቀጣይም የተሻለ ሥነምግባር ያላቸውን ታራሚዎች መልምለን የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ትክክለኛ የእውቀት መፍለቂያ መሆናችንን ለማስመስከር እንሠራለን ሲሉም አክለዋል፡፡

ማረሚያ ቤቶች የመንግሥት ብቻ አይደሉም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዜጎች፣ የተለያዩ ተቋማትና ባለሀብቶች አብረዋቸው እንዲሠሩ ጠይቀዋል።

ማኅበረሰቡም ማረሚያ ቤት የሚገቡ ሰዎች ተለውጠው እንደሚወጡ በማመን እንዲደግፏቸውና ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ አስተላልፈዋል።

# የፕሪቶሪያ የሠላም ስምምነት ውጤቶችና ቀሪ የቤት ሥራዎች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ባለፈው ዓመት በወርሐ ጥቅምት ማገባደጃ ላይ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገውን የፕሪቶሪያ ስምምነት ተከትሎ በትግራይ ለሁለት ዓመታት የቆየው ደም አፋሳሽ ጦርነት ከቆመ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ተሻግሯል።

ሁለቱ ወገኖች ባለ 12 ነጥብ የሠላም ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ ቋሚ የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርጓል፡፡ ስምምነቱ በተለይ ለሁለት ዓመታት ያህል በጦርነት ውስጥ የቆየውን የትግራይ ሕዝብን ጨምሮ ለመላው ኢትዮጵያውያን ታላቅ ተስፋን ሰንቋል።

በክልሉ ተቋርጠው የነበሩ የባንክ፣ የቴሌኮም፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርትና የሰብዓዊ እርዳታዎች እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ ለመሆኑ ከስምምነት በኋላ በተጨባጭ በክልሉ ያለው የሰብዓዊ እርዳታ ድጋፍ፣ የጤና አገልግሎት፣ በወጣቶች ዘርፍና እንዲሁም በመቐሌ ዩኒቨርሲቲ የተከናወኑ ተግባራት፣ የተገኙ ውጤቶችና ቀጣይ መከናወን ያለባቸው ተግባራት ምንድን ናቸው?

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽነር ገብረሕይወት ገብረእግዚአብሔር (ዶ/ር)ለኢፕድ እንደሚገልጹት፤ ከስምምነት በኋላ በክልሉ አብዛኞዎቹ አካባቢዎች አንጻራዊ ሠላም ሰፍኗል፤ እንዲሁም ከፌዴራል መንግሥትና ከድጋፍ ሰጭ ተቋማት ተቋርጦ የነበሩ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የሰብዓዊ እርዳታ ድጋፎች ቀጥለዋል፡፡

በዚህም የፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለአራት ጊዜ ያክል ለተፈናቃዮችና በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በመጀመሪያ ዙር 17 ከተሞችን ተጠቃሚ ያደረገ 31ሺህ 78 ኩንታል እህል ድጋፍ አድርጓል፤ በሁለተኛ ዙር 126ሺህ 15 ኩንታል እህል በተለያዩ ከተሞችና የገጠር ወረዳዎች የሚገኙ ተፈናቃዮችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡

በሶስተኛው 77ሺህ ኩንታል በከፍተኛ ደረጃ በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ድጋፍ መደረጉንና በአራተኛ ዙር ደግሞ 25ሺህ ኩንታል እህል ለተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ተዳርሷል። እንዲሁም በቅርቡ ድጋፍ ላልተደረገባቸው 15 ከተሞች የሰብዓዊ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የፌዴራል መንግሥትም አቅሙ በፈቀደው ልክ ላደረገው ድጋፍ ገብረሕይወት (ዶ/ር) ምስጋና አቅርበው ይህም መታወቅ እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡

አጋር አካላት ከክልከላው በኋላ ካላቸው አቅም 20 በመቶ ብቻ ድጋፍ እያደረጉ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ይህንን የሚያሳድጉበት ሁኔታ እንደሚኖርና በአሁን ወቅት ዜጎች በመኖራቸው ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ይላሉ፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም በተሠራው ሥራ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ተፈናቃዮች ወደየአከባቢያቸው ተመልሰዋል፡፡ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊየን የሚሆኑት ደግሞ በተለያዩ ካምፖች ይገኛሉ፡፡

በክልሉ ጤና ቢሮ የጤና ኤክስቴንሽንና ጤና ማስተዋወቅ ቡድን አስተባባሪ አቶ ሚካኤሌ ሐጎስ እንዳስታወቁት፤ ከግጭቱ በፊት በክልሉ ሁለት ሺህ 500 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የነበሩ ሲሆን አሁን ላይ የሥነ-ልቦና አቅማቸውን የሚያሳድግና ቀድሞ ወደነበሩበት የሥራ መንፈስ መመለስ የሚያስችል ሥልጠና የወሰዱ 1ሺህ ሰባት መቶ ባለሙያዎች ወደ ቀድሞ የሥራ ቦታቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡



እንደ አቶ ሚካኤሌ ገለጻ፤ በጦርነቱ ምክንያት 80 በመቶ የጤና ተቋማት የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፤ ቢሮው ከጤና ሚኒስቴር ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ነው፡፡ በዚህም ሚኒስቴሩ የተጓተቱ የጤና የኤክስቴንሽን ፕሮግራሞችን ለማስጀመር የሚያስችል የአሠልጣኞች ሥልጠና ሰጥቷል፡፡

አፋጣኝ ድጋፍ በሚያስፈልግባቸው ቦታዎች፣ በትምህርት ቤቶችና ዜጎች በብዛት በሚሰባሰቡባቸው አካባቢዎች የሕክምና አገልግሎት እየቀረበ ነው፡፡ በምግብ እጥረት የተጎዱ ሕፃናትን በመለየት ሕክምና የመስጠት ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለወባ፣ ኮሌራና በሌሎች አፋጣኝ በሽታዎች ላይ እየተሠራ መሆኑን አቶ ሚካኤሌ አስረድተዋል።

የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ወጣቶች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሀይሽ ሰባጋዲስ በበኩላቸው፤ በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ ወጣቶች በራሳቸው ሥራ ለመፍጠር የሚፈልጉና ሙከራ እያደረጉ ሲሆን በተለይም ጥቂቶቹ በግብርና ሥራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ እንዲሁም ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በግብረ ሠናይ ድርጅቶች ድጋፍ ሥራ የጀመሩ ወጣቶችም እንደሚገኙ ይገልጻሉ፡፡

የሥራና ክህሎት፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይና የሠላም ሚኒስቴር ወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸውና ሥልጠና እንዲያገኙ በተለያየ መልክ ድጋፎችን እያደረጉ ነው ያሉት አቶ ሀይሽ፤ ከዚህ ቀደም ለወጣቶች የሥራ ዕድል ሲፈጥሩ የነበሩ በፌዴራል መንግሥት የተያዙ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ወደሥራ አለመመለሳቸውና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች አለመጀመራቸው ችግር ሆኗል ይላሉ፡፡

አቶ ሀይሽ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ የፀጥታ ሁኔታን በመጠራጠር በከፍተኛ ቁጥር የወጣቶች ስደት እየተከሰተ ነው፤ 19 በመቶ ወርዶ የነበረው የወጣቶች የሥራ አጥ ቁጥርም ከግጭቱ በኋላ በመቐሌ ዩኒቨርሲቲ በተሠራ ጥናት 81 በመቶ ከፍ ማለት ችሏል፡፡

የመቐሌ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ፋካሊቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓብድልቃድር ከሪም እንዳሉት፤ ዩኒቨርሲቲው ዘንድሮ ከ2ሺ በላይ ተማሪዎችን አስመርቋል፤ አሁን ላይ ከ11ሺ በላይ ተማሪዎችን እያስተማረ ሲሆን የመጀመሪያ አጋማሽ አልቆ ሁለተኛ ሴሚስተር የመማር ማስተማር ሂደቱ እየቀጠለ ይገኛል፡፡

ፕሬዚዳንቱ እንደሚሉት፤ ዩኒቨርሲቲው ለ2016 ዓ/ም በጀት ዓመት ባስቀመጠው ዕቅድ መሠረት የሪፎርም ሥራዎችን ሠርቶ በማጠቃለል ላይ የሚገኝ ሲሆን ተማሪዎች ማስመረቁ እንዲሁም አዳዲስ ተማሪዎች መቀበሉ እንደ ጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፡፡ ሆኖም ግን ለምርምርና ለላብራቶሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እጥረትና የተማሪዎች ኢንተርንሽፕ ከማሳካት አንፃር የበጀት እጥረት ክፍተት ይታያል፡፡

ለመማር ማስተማር ሂደቱ እንደ እንቅፋት የሆነው የበጀት እጥረት በተለይ ለአስተማሪዎች ተገቢውን ሁሉ እንዲሟላላቸው፤ እንዲሁም ተማሪዎች ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ በተግባር ትምህርት ተገቢውን ዕውቀት ለማግኘት እገዛ ስለሚኖረው ክፍተቱ ለቀጣይ እንደሚፈታ ዶክተር ዓብድልቃድር ያነሳሉ፡፡

# በዞኑ ከ90 በመቶ በላይ መሬት አሲዳማ መሆኑን ጥናት አረጋገጠ

**ማርቆስ በሳይ**

አዲስ አበባ፡- በዞኑ በዘንድሮው ዓመት ከአራት ሺህ 100 አርሶ አደር ማሳ በተወሰደ የአፈር ናሙና ከ90 በመቶ በላይ በአሲዳማነት የተጠቃ መሆኑን የጂማ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጂማ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መሐመድጠሀ አባፊጣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በዘንድሮው ዓመት ከአራት ሺህ 100 አርሶ አደር ማሳ የአፈር ናሙና ተወስዶ ጥናት ተደርጎበታል፡፡ በዚህም አፈሩ ከ90 በመቶ በላይ በአሲዳማነት የተጠቃ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በጂማ ዞን መሬትን ለማከም የተፈጥሮ ማዳበሪያና ኮምፖስት ላይ በስፋት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ መሀመድጠሀ፤ ከ350 ሺህ በላይ ዝርሚ ኮምፖስት፣ 15 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ መደበኛ ኮምፖስት ማምረት ተችሏል ብለዋል፡፡

የአፈር አሲዳማነትን ለማከም በመደበኛና የተፈጥሮ ማዳበሪያ አማካኝነት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው የጂማ ዞን ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኝ በመሆኑ በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ መሬት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ክልል የግብርናው ዘርፍ ችግሮች ምንድናቸው በሚል ጥናቶች መካሄዳቸውን በመግለጽ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት አፈርን በማከም ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በዘንድሮው ዓመት አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን የኅብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት የተፋሰስ ልማት በ510 ቀበሌዎች 510 ተፋሰሶች ተለይተዋል ያሉት አቶ መሀመድጠሀ፤ 255 ሺህ ሄክታር መሬት በተፋሰስ ልማት ለመሸፈን የተለያዩ ውሃን የሚያቁሩ እርከኖችን እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ክልል የአፈር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ኢኒሼቲቭ ተቀርጾ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካትን ጨምሮ ወደ ውጪ መላክና በዘርፉ የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡


አቶ መሐመድጠሀ አባፊጣ

ዜና

# የ2016 ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢንቨስትመንቶችን መሳብ፣ በአምራቾች መካከል የልምድ ልውውጥ እና የገበያ ትስስር መፍጠር መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በኤክስፖው ላይ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስ ትሪዎችን ጨምሮ በአምራች ዘርፉ የሚሳተፉ 230 ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ይዘው የሚቀርቡ መሆኑን ገልጸው፤ የገበያ ትስስር በመፍጠር ከ2 ቢሊዮን በላይ ብር የምርትና ቴክኖሎጂ ግብይት እንደሚካሄድ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በዚህ ዓመት በአጠቃላይ ወደ 100 ሺህ ጎብኚዎች እና 600 ሺህ ተጋባዥ እንግዶች በኤክስፖው ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም አያና (ዶ/ር) አመላክተዋል፡፡

በኤክስፖው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ከተጀመረ ጀምሮ የአምራች ኢንዱስትሪውን በመደገፍ በኩል የተሠሩ ሥራዎች፣ ለሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ተሳታፊዎች የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሄደበትን መንገድ የማሳየት፣ አሁን ያለው አዲሱ ፖሊሲ የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል ብለዋል።

እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪዎቹ ያሉባቸውን ማነቆዎችና የባለድርሻ አካላትን ችግሮችን ከመፍታት አንጻር እስካሁን ያደረጉት አስተዋፅዖ፣ አዲስ የመፍትሔ ሀሳቦች የሚዘጋጅበት ሲሆን የፖሊሲ አውጪዎችና ሰብሳቢዎች፣ ምሑራን እና ከግል ሴክተሩን የተወጣጡ የሚሳተፉበት የውይይት መድረክ እንደሚኖርም ገልጸዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከ450 በላይ ተጋባዥ እንግዶች እና ከ50 ሺህ በላይ ጎብኚዎች በመታደም 1 መቶ 25 የግብይት ትስስር በመፍጠር ወደ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ተፈጽሞ እንደነበርም አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ለ10 ዓመታት የሚካሄድ ሲሆን ባለፉት ሁለት ዓመታትም የአምራች ዘርፉን መደገፍ ቁልፍ አጀንዳ የማድረግ፣ አምራች ኢንቨስትመንት በኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረውን ድርሻ የማሳደግ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም የሀገር በቀል ኢኮኖሚውን በቅንጅታዊ አሠራር በመደገፍ ረገድ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም አምራች ኢንዱስትሪው ከፋይናንስ፣ ከግብዓት፣ ከመሠረተ ልማት፣ ከሰው ኃይል ረገድ ያለባቸው ችግሮች በመለየት የመፍታት ሥራ የተሠራ ሲሆን፤ በዚህም ከዚህ በፊት ማምረት አቁመው ከነበሩ 446 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 390 ኢንዱስትሪዎች ወደ ማምረት እንዲገቡ የተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም በትግራይ ክልል በጦርነት የተጎዱ በአጠቃላይ 217 አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንደስትሪዎች ማምረት የጀመሩበት ሁኔታ እንዳለም አያና (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

በፋይናንስ አቅርቦት በኩል ለአምራቹ ዘርፍ ከ12 በመቶ በታች ይሰጠው የነበረን የብድር አቅርቦት በዚህ ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ ወደ 13 ነጥብ 8 በመቶ በማሳደግ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ዓመት የብድር አቅርቦቱን 24 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያና ታንዛኒያ የአቪዬሽን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያበቃ፣ የተደራጀና ጠንካራ ተቋም ነው። ከአዲስ አበባ-ዳሬ ሰላም በረራውን የጀመረው በ1966 ሲሆን በታሪክ በኪሊማንጃሮ በረራ ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመረም ነው፡፡

በአቪዬሽን መስክ ያሉ ትብብሮች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ያሉት አምባሳደሩ፤ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ በታንዛኒያ ባሉ ሦስቱም ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች በዳሬ ሰላም፣ በዛንዚባርና በኪሊማንጃሮ በሳምንት ከ42 በላይ በረራዎችን ያደርጋል።

ታንዛኒያ በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻ ሀገር ስትሆን ታንዛኒያን ለመጎብኘት ለሚንቀሳቀሱ ጎብኚዎች ምቹና ቀልጣፋ የበረራ አገልግሎትን በመስጠት አየር መንገዱ ለታንዛኒያ የቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ሚና እየተወጣ ይገኛል።

ይህንን ለማጠናከር የታንዛኒያ ቱሪዝም ቦርድ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የመግባቢያ ሰነዶች መፈራረሙንም አምባሳደር ሽብሩ ጠቅሰዋል፡፡

# የኅብረተሰቡ የጤና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ሰባት ሆስፒታሎችና ከአንድ መቶ በላይ ጤና ጣቢያዎች ለዜጎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል የሚገለገልባቸው ጤና ጣቢያዎች ለዜጎች ጥራት ያለውን የጤና አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ለማሳደግ ምን እያከናወኑ ነው? ተገልጋዮችስ ምን ይላሉ?

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የማይጨው ጤና ጣቢያ ምክትል ሜዲካል ዳይሬክተር አበበ ሣሕሌ እንደሚናገሩት፤ ጤና ጣቢያው ከአስር ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ አድማሱን በማስፋት ባለንበት ወቅት ከ31ሺህ በላይ ለሆኑ አባወራዎች አገልግሎት እየሰጠ ነው፤ ከጉለሌ በተጨማሪ ከአራዳና ከየካ ክፍለ ከተሞች የሚመጡ ዜጎችንም ያስተናግዳል፡፡

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ ተቋሙ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ተከትሎ የአስተኝቶ ማከም፣ የመለስተኛና የእናቶችን በቀዶ ጥገና የማዋለድ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ በክፍለ ከተማው ከሚገኙ አቻ ተቋማት ቀዳሚ ያደርገዋል፡፡ በአዲስ አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ የማኅበረሰብ የጤና መድኅን አገልግሎት የተሞከረበትና ግልጸኝነት ያለው የፋርማሲ አሠራር ተግባራዊ የተደረገበት ተቋም ነው፡፡

የጤና ተቋሙ ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት እያሰፋ በመምጣቱ አዲስ የማስፋፊያ ፕሮጀክት አስፈላጊ በመሆኑ በአሁን ወቅት ባለ ሦስት ወለል የማስፋፊያ ግንባታ በመከናወን ላይ ነው፡፡ ግንባታው ሲጠናቀቅም ከአንገት በላይ የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ የእናቶችና የሕጻናት ሕክምናን ስፔሻላይዝድ ለማድረግ መታሰቡን አቶ አበበ ይጠቅሳሉ፡፡

አገልግሎቱ በሚሳለጥበት ወቅት ከሕክምና ግብዓት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚገጥሙ ችግሮች በመኖራቸው ለከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ ከማሳወቅ በተጨማሪ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አጋር ድርጅቶችን የማፈላለግ ተግባር እየተከናወነ ነው የሚሉት አቶ አበበ፤ በቀጣይም የተቋሙ ባለሙያዎች ቤት ለቤት እየሄዱ የሚሰጡትን ጤና አገልግሎት በማጠናከር ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ለመሆን ውጥን መያዙን ይጠቅሳሉ፡፡

በማይጨው ጤና ጣቢያ የሕክምና ክትትል እያደረጉ ከሚገኙት ነፍሰ ጡር ባለቤታቸው ጋር ያገኘናቸው አቶ ፀጋዬ አጽበሐ፤ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከትላልቅ ሆስፒታሎች እንደማይተናነሱ ጠቁመው፣ ለዚህም ከወሊድ ጋር በተያያዘ በርካታ ተገልጋዮች ወደተቋሙ እየመጡ እንደሆነ መመልከታቸውን ይናገራሉ፡፡

ከዚህ ቀደም በሌላ ተቋም ሕመምተኞችን ያለመጎብኘት ችግር ተመልክቻለሁ የሚሉት አቶ ፀጋዬ፤ በማይጨው ጤና ጣቢያ እንዲህ አይነት ችግር እንዳላዩና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ በመምጣት ለባለቤታቸው አስፈላጊውን ክትትል እያደረጉ በመሆኑ በአሁን ወቅት ባለቤታቸው በጥሩ ጤንነት ላይ እንደምትገኝ ይገልጻሉ፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የአፍንጮ በር ጤና ጣቢያ በ2004 ዓ.ም የተመሠረተ ነው፡፡ ሥራ አስኪያጁ ደነቀ ፀጋ እንደሚናገሩት፤ ጤና ጣቢያው በዙሪያው የሚገኙትን ከ40ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች እያገለገለ ይገኛል፡፡ የነፍሰ ጡር ክትትል፣ የቲቢ፣ የኤች አይቪ ምርመራ፣ በቀዶ ጥገና የማዋለድና ሌሎችንም አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

ተቋሙ ፆታዊ ጥቃት ደርሶባቸው ለሚመጡ ሰዎች ሙሉ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት የሥነ ልቦና ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ በዚህም ከፖሊስና ከዐቃቤ ሕግ ጋር በመሆን ጉዳት ያደረሰውን አካል ለፍርድ እንዲቀርብ የማድረጉንም ሥራ እየተሠራ መሆኑን አቶ ደነቀ ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ደነቀ ገለጻ፤ ተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመንና የተገልጋዮችን እንግልት ለመቀነስ እንዲያስችል በተያዘው ዓመት የወረቀት አልባ ሥራዎች ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡ አገልግሎት እየሰጠባቸው ከሚገኙት መሣሪያዎች በተጨማሪ የኤክስ ሬይ ማሽንና ሌሎችንም በመጠቀም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የግዢ ጨረታ አውጥቷል፡፡

ኅብረተሰቡ ስለተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ያለውን እሳቤ እንደግብዓት በመውሰድ የዜጎችን ችግር ለመፍታት ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ምንም እንኳን ሀገራዊ ቢሆንም የበጀት ማነስ ትልቁ ችግራችን ነው ያሉት አቶ ደነቀ፤ የምርመራ ማዕከል ለመክፈት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለማስፋፊያ ግንባታ ተጨማሪ ቦታ እንዲሰጥ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ቀርቧል ብለዋል፡፡

በተቋሙ በቀጣይ የጆሮ፣ የዓይን፣ የጥርስና ሌሎችም ስፔሻሊቲዎች እንደሚከፈቱ፤ ከየካቲት 12 ሆስፒታል ጋር በመሆን በሕጻናትና በሰሪጀሪ ላይ የሚሠሩ የሕክምና ባለሙያዎች በሳምንት ለሁለት ቀናት በጤና ጣቢያው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ እንዲሁም የሙሉ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ከራስ ደስታ ሆስፒታል ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን አቶ ደነቀ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ ቀደም በሌላ የጤና ተቋም የወሊድ ክትትላቸውን ያደርጉ የነበረ ቢሆንም ተገቢውን አገልግሎት እያገኙ ባለመሆኑ ወደአፍንጮ በር ጤና ጣቢያ እንደመጡ የሚናገሩት ወይዘሮ መሠረት ታምራት፤ ወደዚህ በመምጣታቸው ለእሳቸውም ሆነ ለልጃቸው የሚበጅ እንክብካቤ እንዳገኙ ይናገራሉ፡፡

በጤና ጣቢያው በሚያገኙት አገልግሎት ደስተኛ መሆናቸውን የሚገልጹት ወይዘሮ መሠረት፤ በተሰጠኝ የሕክምና አገልግሎት ልጄ በፍጹም ጤንነት ላይ ይገኛል ይላሉ፡፡ አክለውም እናቶች በወሊድ ወቅት የስሜት ከፍታና ዝቅታ የሚገጥማቸው በመሆኑ ያልተገባ ጭንቀት ውስጥ እንዳይገቡ ለእነሱና ለልጆቻቸው የሚሰጠው እንክብካቤ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡



ፈቶ ኢስሞ (ዶ/ር)

# የብርዕ፣ የአገዳና የጥራጥሬ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተጠናከረ ሁኔታ እየተሠሩ ነው ሲል የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ፈቶ ኢስሞ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በብርዕ፣ በአገዳና በጥራጥሬ ሰብሎች ላይ አዳዲስ ዝርያዎችን በማፍለቅ ለሀገር አርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግና ምርታማነት ለማሳደግ ከዚህ በፊት ከነበረው የምርምር ሥራ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው፡፡

ተቋሙ በብርዕ፣ በአገዳና በጥራጥሬ በአምስት ሰብሎች ማለትም በስንዴ፤ በገብስ፣ በጤፍ፣ በማሽላና በቆሎ ላይ የዝርያ የማሻሻል ሥራ በመሥራት የአርሶ አደሩን ፍላጎት 95 በመቶ ለማሟላት ከሌሎች ሰብሎች የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ የምርምር ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለውም አዳዲስ ቴክኖሎጂን የማፍለቅ ሥራ የሀገርን ምርትና ምርታማነትን በእጥፍ የሚያሳድግ ነው ብለዋል፡፡

የብዕር፣ የአገዳና የጥራጥሬ ሰብሎችን የማሻሻል ሥራ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርምር ውጤታማ በማድረግ የአርሶ አደሩን የምርጥ ዘር አጠቃቀም ፍላጎትን በበቂ ሁኔታ ለመሸፈንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሀገሪቱን የግብርና ዘርፍ ለማዘመን፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ በሕዝብ እድገት ልክ ግብርናውን ለማሳለጥ የግብርና የምርምር ሥራና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ ሥራ በተጠናከረ መንገድ መሥራት አስፈላጊ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ ምርትና ምርታማነትን ይበልጥ ለማሳደግ በብዕር፣ በአገዳና በጥራጥሬ ሰብሎች ላይ የተለያዩና ለየት ያሉ ምርምሮች እየተሠሩ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከግብርና ዘርፍ ለማሳደግ ከዚህ በፊት የሀገሪቱን የአየር ንብረት ግምት ውስጥ የሚያስገቡና የአየር ፀባዩን የሚላመዱ የሰብል ማሻሻያ ሥራዎች ይሠሩ እንደነበር የገለጹት ፈቶ (ዶ/ር) በአሁን ሰዓት እየተሠሩ ያሉ ምርምሮች የአየር ንብረቱን መላመድ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ምርት የሚያስገኙ ናቸው ብለዋል፡፡

በተቋሙ እየተሠሩ ያሉት የተለያዩ የስብል የምርምር ሥራዎች እንደ ሀገር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው ሥራ ላይ ትልቅ ውጤት እያስገኙ ነው፤ እየተሠሩ ያሉ ምርምሮችም አትክልቶችንና ፍራፍሬዎች እንዳይበላሹ ከሚያደርግ የምርምር ሥራ ወደ ሰብል ዘረመል ማሻሻል ተሸጋግሯል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በሽታን፣ ድርቅን መቋቋም የሚችሉ የሰብል ዝርያዎችን በምርምር በማግኘት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራበት በመሆኑ ሀገሪቱ በስንዴ ምርት ራሷን ችላለች ብለዋል፡፡

“የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለግብርናው ግብዓት ለማድረግ የሚሠራው ሥራ እያደገና እየዘመነ መጥቷል፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ ሥራ ከዚህ በፊት አስር ሄክታር መሬት ላይ ብቻ ነበር ዘር የሚዘራው፤ አሁን ወደ ኩታገጠም ከፍ እንዲል ሆኗል” ያሉት ዳሬክተሩ የቴክኖሎጂ ግኝትን አርሶ አደሩ በሚፈልገው ልክ አባዝቶ ተደራሽ ለማድረግ የመሬት እጥረት እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከትናንት ስህተቶቻችን ለመማር ዝግጁ እንሁን !

እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሄድባቸው የነፃነት፤ የፍትሕ፣ የአትንኩኝ ባይነት የደመቁ ታሪኮች ባለቤት የመሆናችንን ያህል አንገት የሚያስደፋ፤ የሚያሳቅቁ እና ምንነካቸው የሚያስብሉ ታሪኮችም ባለቤት የመሆናችን እውነታ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በተለይም የብዙ ሺ ዓመታት የሀገረ መንግሥት ምሥረታ ታሪክ ባለቤት ከመሆናችን ጋር ተያይዞ፤ እንደ ሀገር የሚፈጠሩ የፖለቲካ ልዩነቶቻችን በሠላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት ባለመቻላችን በዚህም ያልተገቡ ዋጋዎችን ለመክፈል የተገደድንባቸውን ብዙ ታሪካዊ ክስተቶች አሳልፈናል ።

የሩቁን ትተን የቅርቦቹን የግጭት ታኮዎቻችንን እንኳን ለማየት ብንሞክር፤ ብዙ ተስፋ እና ሀገራዊ ራዕይ ሰንቆ የተንቀሳቀሰው የስልሳዎቹ ትውልድ አንድ አይነት ቋንቋ እየተናገረ፤ በሰከነ መንፈስ፤ በተረጋጋ አዕምሮ ቆም ብሎ መነጋገር ሳይችል በመቅረቱ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የከፋ የሚባል ጥቁር ጠባሳ ጥሎ ለማለፍ ተገድዷል።

ያ እንደ ሀገር ብዙ ተስፋ የተጣለበት ትውልድ፤ የተነሳበትን ትልቁን ሀገራዊ ራዕይ፤ ሀገርና ሕዝብን ከኋላቀርነትና ከድህነት ለማሻገር አስቦ እና በብዙ አምጦ የጀመረውን የመለወጥ ትግል ረስቶ በጠላትነት ተፈራርጆ፤ በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ላልተገባ እልቂት እና ለስደት ተዳርጓል። በዚህም ሀገርና ሕዝብ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል አድርጎታል ።

በቀጣይ የነበሩት ስድስት አስርት ዓመታትም እንደ ሀገር በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት የተገዛው የፖለቲካ አስተሳሰባችን፤ አሸናፊዎችን የፖለቲካ መንበር ላይ ከማስቀመጥ ባለፈ፤ ዘላቂ የሆነ የፖለቲካ መረጋጋት ሊያመጣ አልቻለም። ከዛ ይልቅ ሀገርን እንደ ሀገር ወደብ አልባ የሚያደርግ ታሪካዊ ስህተት እንዲፈጠር አድርጓል ።

ከዚህም ባለፈ፤ እንደ ሀገር ለዘመናት በትውልዶች ቅብብሎሽ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመውን ሀገራዊ አንድነት፤ በተለያዩ የልዩነት ትርክቶች በመሸርሸር፤ ብሔራዊ አንድነታችን ሆነ በአጠቃላይ ሀገረ መንግሥቱ ስጋት ውስጥ የሚገባበትን አደጋዎች ይዞ መጥቷል። የታሪካዊ ጠላቶቻችን የማይቆም ሴራ ሰለባ እንድንሆንም አድርጎናል ።

ከዚህ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ ካስከፈለን፤ የቅርብ ጊዜ ስህተታችን መማር አለመቻላችን ትናንት ላይ ተመሳሳይ ስህተት በመሥራት ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል የተገደድንበት ታሪካዊ ክስተት ውስጥ እንድንገኝ አድርጎናል። እንደ ቀደመው ጊዜ በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት /በይዋጣልን /መንገድ ሄደን ዛሬዎቻችንን ጭምር የስህተታችን ጥላ ሰለባ እንዲሆኑ አድርገናል።

ይህ በዘመናት መካከል ትውልዶችን ዋጋ እያስከፈለ ያለ የተበላሸ የፖለቲካ አስተሳሰብ፤ አንድ ቦታ መቆም ካልቻለ፤ እንደ ሀገር የሚኖረን ቀጣይ ዕጣ ፈንታችን ከቀደመው ዘመን ከነበርንበት የከፋ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን፤ ከተለመደው የግጭት አዙሪት አውጥቶ ሀገር አልባ ሊያደርገን እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይደለም ።

በተለይም የመልማት መሻታችን፤ ለመሻታችን ያለን ቁርጠኝነት እና አሁን ላይ በተጨባጭ እያስመዘገብነው ያለው ስኬት፤ መልማታችንን እንደ ስጋት ለሚያዩ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ሆነ ለሌሎች ኃይሎች የጥፋት ሴራ ትልቅ አቅም እየሆነ እንደሚገኝ ከየእለት ተግባራቸው እያስተዋልነው ያለ እውነታ ነው።

የቀደሙትን ትውልዶች ራዕይና ሀገራዊ ተስፋ የተናጠቀ ይህ ኋላ ቀርና ዘመኑን የማይዋጅ የፖለቲካ እሳቤያችን፤ በተመሳሳይ መልኩ የዚህን ትውልድ ሀገራዊ ራዕይና ተስፋ እንዳይናጠቅ፤ ትውልዱንም እስካሁን ካስከፈለው ያልተገባ ዋጋ በላይ እንዳያስከፍለው ቆም ብለን ነገሮችን ተስፋ አድርጎ እንደሚጠብቅ ትውልድ በሰከነ መንፈስ ልናስብ ይገባል።

ከየትኛውም አይነት የይዋጣልን፤ የእልህ እና የስሜት መንገድ ወጥተን፤ ችግሮቻችንን በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለን በመነጋገር የምንፈታበትን በእጃችን ያለ አማራጭ ልንጠቀም ይገባል። ለዚህ ዘመኑን ለሚዋጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተገዥ በመሆን እንደ ሕዝብ ከግጭት አዙሪት የምንወጣበት አስቻይ ሁኔታ ልንፈጥር ያስፈልጋል ።

እንደ ሀገር ወደምንመኘው ብልጽግና ልንጓጓዝ የምንችለው፤ ብዙ አንገት የሚያስደፋ ሀገራዊ ትርክቶች ባለቤት ካደረገን፤ ከአሸናፊ ተሸናፊ የፖለቲካ ትርክት እሳቤ ወጥተን ልዩነቶቻችንን በድርድርና በውይይት መፍታት የሚያስችል ሀገራዊ የፖለቲካ ዓውድ መፍጠር ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ከትናንቶች ተምሮ እራሱን ሊያዘጋጅ ይገባል። እንደ ሀገር የተሻሉ ነገዎች የሚኖሩን ይህንን ስናደርግ ብቻ ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኮሪደር ልማት እና አዲስ አበባን ዘመናዊ ከተማ የማድረግ ጅማሮ

ግርማ ሞገስ

አዲስ አበባ የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች፤ ቆንስላዎችና ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ መቀመጫ ናት፡፡ ታዲያ ይህን ሚና የያዘች ከተማ ብትሆንም እንደእድሜዋ ያልዘመነች፤ ለነዋሪዎች ምቹ ያልሆች ከተማ እየተባለች ትተቻለች፡፡ በቅርቡ ከተማዋን ለማዘመን፤ ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የከተማ አስተዳደሩ የኮሪደር ልማት በሚል ፕሮጀክት ነድፎ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባን ገጽታ አጉድፈው ከሚያሳዩ ስፍራዎች መካከል እንደ «ዶሮ ማነቂያ እሪ በከንቱ፤ ፒያሳና ሌሎች ወንዝ ዳርና የመንገድ ኮሪደሮች» ይገኙበታል፡፡ ለመልሶ ግንባታና የኮሪደር ልማት ተነሺዎች ተመጣጣኝ የገንዘብና የመሬት ካሣ አቅርቦት ተዘጋጅቶ የማስተናገድ ሥራ እየተሠራ ነው ፡፡

ልማቱ መንግሥት አዲስ አበባን እንደስሟ ውብ አበባ ለማድረግ ቀደም ሲል የገባውን ቃል መሠረት አድርጎ የሚከናወን፤ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ግዙፍና ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችን የሚያካትት ነው።

እስካሁን ከተሠሩት የልማት ሥራዎች መካከል ማዘጋጃ ቤት፣ መስቀል አደባባይ፣ ወንድማማችነትና አንድነት ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም አብርሆት ቤተ መጽሐፍት፣ ፑሽኪን አደባባይ፣ ጎተራ አቃቂ ቦሌ መንገድ ግንባታ የመሰሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚህ ግንባታዎች ለከተማዋ ልዩ ገጽታ ከማጎናጸፋቸው በተጨማሪ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋጽዖ እያበረከቱ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው አዲስ አበባን ለቱሪዝም ምቹ እና ውብ የማድረግ የኮሪደር ልማትም የዚሁ ልማት ቀጣይ ምዕራፍ ነው፡፡

በመጀመሪያ ዙርም በዓድዋ ድል መታሰቢያ ፒያሳ-አራት ኪሎ-ቀበና-መገናኛ፤ አራት ኪሎ-ቦሌ አየር ማረፊያ-ቦሌ ድልድይ-መገናኛ፤ ከመገናኛ-አዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ማዕከል ሲኤምሲ እንዲሁም ከሜክሲኮ-አፍሪካ ኅብረት-ሳር ቤት ወሎ ሰፈር 40 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

የኮሪደር ልማቱ በከተማዋ ለነዋሪዎች ምቹ ያልሆኑ፣ ለአደጋና ለበሽታ የሚያጋልጡ አካባቢዎችን እንዲታደሱ የማድረግ የልማት ሥራን ማዕከል ያደረገ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ሲገለጽ ይደመጣል፡፡

ምንም እንኳ የልማቱን አስፈላጊነት ለኅብረተሰቡ በተገቢው መንገድ የማስገንዘብ ሥራ ውስንነት ቢኖረውም የልማት ተነሽ የኅብረተሰብ ክፍሎች መነሳታቸው የተሻለ መኖሪያ አካባቢ እንዳገኙ ይገልጻሉ፡፡

> ምንም እንኳ የልማቱን አስፈላጊነት ለኅብረተሰቡ በተገቢው መንገድ የማስገንዘብ ሥራ ውስንነት ቢኖረውም የልማት ተነሽ የኅብረተሰብ ክፍሎች መነሳታቸው የተሻለ መኖሪያ አካባቢ እንዳገኙ ይገልጻሉ

የተለያዩ ዘገባዎች እንደሚያመላክቱት፤ በኮሪደር ልማት ሥራው ለሁሉም ማኅበረሰብ ምቹ የጋራ መጠቀሚያ ከመፍጠር ያለፈ የሚቀየር የመዲናዋ የአካባቢ ስያሜ የለም። በኮሪደር ልማት ሥራውም ቅርሶችና መሠረተ ልማቶችን የመንከባከብ፣ የመጠበቅና የማደስ ሥራ በማከናወን በነበሩበት እንዲቀጥሉ ይደረጋል። ይህም ከዓለም አቀፍ ከተማ ጋር ተወዳዳሪ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡

በቅርስነት የተለዩ እንደሲኒማ ኢትዮጵያ፣ ሀገር ፍቅር፣ ሸዋ ሆቴል፣ ሲቲ ኮንቬንሽን፣ የሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ቤት፣ የቀድሞዎቹ ማዘጋጃና ፖስታ ቤት ታድሰው ባሉበት ይቀጥላሉ ተብሏል። ይህም አልፎ አልፎ በአንዳንድ «አክቲቪስቶች» ዘንድ የሚነዛውን የሐሰተኛ መረጃ ያከሸፈ ነው፡፡

የልማት ተነሽዎች ባሉበት አካባቢ ባሉ ክፍለ ከተሞች የኮሪደር ልማት ክትትል ግብረ ኃይል እንዳለና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለአምስቱም የኮሪደር የልማት ተነሺዎች ቅሬታ ምላሽ የሚሰጥ ጽሕፈት ቤት መኖሩ ለሚነሱ ቅሬታዎች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

የነዋሪዎችን ማኅበራዊ ትስስር ለማስቀጠልም በድኅማ የሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል መኖሩም አብሮነታቸውንን ለማስቀጠል ምቹ አጋጣሚ ነው፡፡ ይህም ልማቱ የማኅበረሰቡ ማኅበራዊ መስተጋብር እንዲቀጥልና በልማቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጥርባቸው የሚያደርግ ነው፡፡

የኮሪደር ልማቱ ካለው ስፋት አንፃር በፒያሳ፣ አራት ኪሎና ቦሌ መስመር የመንገድና የአረንጓዴ ልማት ሥራውን እስከ ግንቦት መጨረሻ ለማጠናቀቅ በትኩረት በመሥራት ላይ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና ድንገተኛ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን መረጃ እንደሚያመላክተው፤ የመዲናዋ የኮሪደር ልማት ከከተማ ልማትም ባለፈ ለእሳትና ድንገተኛ አደጋ ተጋላጭ የነበሩ ዜጎችን ሊታደግ የሚችል ነው፡፡

ከቤቶች ግንባታ ጥግግት፣ ከመንገዶች ጥበት፣ ከኤሌክትሪክ ማስተለለፊያ ገመዶች መደራረብ እና ከፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች መደፈን ጋር የሚከሰቱ አደጋዎችንም ለመከላከል እየተከናወነ ያለው የመንገድ ኮሪደር ልማት የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው።

የኮሪደር ልማቱ ቤቶች በፕላን እንዲገነቡ፣ መንገዶች እንዲሰፉ፣ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታና የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በጥራት እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው። በርካታ አካባቢዎችን ከእሳት ቃጠሎ፣ ከጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ከትራፊክ መጨናነቅና ሌሎችም አደጋዎች የታደገ ሁነኛ መፍትሔ ይሆናል ተብሎም ይታመናል፡፡

የኮሪደር ልማቱ የአዲስ አበባ ከተማን ታላቅነትና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ ከተማ ለማድረግ፣ ስሟን የሚመጥን ለማድረግ እና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የተጀመረ የመልሶ ግንባታ ሥራ ስኬታማ እንዲሆን የሁሉም አዎንታዊ ትብብር ወሳኝ ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# ፍትሐዊነትን የሚያረጋግጠው የኢትዮጵያውያን አሻራ

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)

መነሻውን ሰከላ ያደርጋል። መዳረሻውን ደግሞ ከ6 ሺህ 700 ኪሎ ሜትሮችን ረጅም ጉዞ በኋላ ሜዲትራኒያን ባህር ላይ ያደርጋል። ሽንጠ ረጅም ነው። ከትንሿ ምንጭ ሰከላ ተነስቶ ከገባሮቹ ጋር እያበረ አስራ አንድ የሚሆኑ ተፋሰስ ሀገራትን አስተሳስሮ ከጥልቁ ባህር ጋር ይቀላቀላል። 86 ከመቶ ያህሉን የውሃ ድርሻም ከኢትዮጵያ ያገኛል። የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ፤ ዓባይ። ይህ ወንዝ ለአንዳንድ ሀገር ልምላሜም፤ ለቀሪዎቹ ደግሞ የዘመናት ተስፋን ሲሰጥ ዘመናት ተቆጥረዋል። ለምዕተ ዓመታት ያልተቋጨ ንትርክም በዚህ ወንዝ ጉዳይ ተሰምቷል።

ዓባይ ፍትህና ሚዛናዊነት ተንጸባርቆበት ሁሉንም ተፋሰስ ሀገራት ተጠቃሚ ሲያደርግ አልታየም። ሆን ተብሎ በተደረገ አግላይ ስምምነት እንደ ግብጽ ያሉ ምንም ድርሻ የሌላቸውን ሀገራት ተጠቃሚ ሲያደርግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላትን ኢትዮጵያንም አግልሎ የበይ ተመልካች አድርጓት ለዘመናት ቆይቷል።

በግብጽ መንግሥት በኩል እየተስተዋለ ያለው የአንድ ወገንን ተጠቃሚነት የሚያንጸባርቅ አካሄድ ከታሪክ አንጻር ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበትን የ1929 እና የ1959 ስምምነትን እንደመነሻ ወስዶ የሚሞግት ነው። ባለፉት ዓመታት የሶስትዮሽ ድርድሩ በሁለት እግሩ እንዳይቆም እንቅፋት ከፈጠሩ ሁነቶች ውስጥ ይሄ ነፍጥ እና ራስ ወዳድነትን ያነገበ ኢ-ፍትሐዊ የታሪክ ስምምነት ተጠቃሽ ነው።

ግብጽ በዓባይ ላይ ያላት የበላይነት እንዴት ተረጋገጠ? እንዴትስ ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበት ስምምነት ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ዘመነ ቅኝ ግዛትን ነው። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያና መገባደጃ ላይ አፍሪካውያን በበርካታ የአውሮፓ ሀገራት ቅኝ ግዛት ስር ነበሩ። በዚህም ታላቋ ብሪታንያ የግብጽ ገዢ ሆና ወደ ርስቷ ስትገባ ደካማ ጎኗን በማሰብ ጭምር ነበር።

እንግሊዛውያን የግብጽ ደካማ ጎን የዓባይ ወንዝ መሆኑን ለማወቅ ብዙ አልተቸገሩም። በዚህም መረዳት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የተፋሰስ ሀገራት ያልተሳተፉበትን ሁለት ስምምነቶች አድርገዋል። የመጀመሪያው ስምምነት እ.ኤ.አ ግንቦት 7 ቀን 1929 በግብጽና በቅኝ ገዢዋ በእንግሊዝ መካከል የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት ነው።

በዚህ ስምምነት ውስጥ ዓባይ በሚለው ታሪክ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ሌሎች የተፋሰስ ሀገራትን ባላማከለ መልኩ የግብጽን የብቻ ተጠቃሚነት የሚያውጅ ነበር። በዚህም ግብጽ 48 ቢሊዮን ኪዩቢክ የሚሆነውን የውሃ መጠን ስትጠቀም የሱዳን የውሃ ድርሻ 4 ቢሊዮን ኪዩብክ ብቻ ነበር።

ይሁን እንጂ በሱዳን ውትወታና የይገባኛል ጥያቄ ግብጽ ለሁለተኛ ጊዜ ስምምነት ማድረጓ ግድ ሆነ። ከሰላሳ ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ ህዳር 8 ቀን 1959 ሱዳንን ያማከለ ሌላ ስምምነት በቅኝ ገዢዋ በእንግሊዝ በኩል ለሁለተኛ ጊዜ ተደረገ። ይሄ ሲሆን በዓባይ ወንዝ ላይ ከ86 ከመቶ በላይ ድርሻ ያላትን ኢትዮጵያን ፍፁም ያገለለ ነበር። ይህ ሸፍጥ ለግብጽ የልብ ልብን በመስጠት ከፍትህና ከእውነት እንድትርቅ ከማድረጉም በላይ ራሷን ብቸኛ ተጠቃሚ አድርጋ እንድታምን የሚያደርግ የተዛባ ትርክት እንድትጠለፍ አድርጓታል ።

ስምምነቱ ታሪካዊና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋትን የጣሰ ስለመሆኑ እንደማስረጃ የሚቀርበው ሌሎች የተፋሰስ ሀገራትን ባላገናዘበ መልኩ ለግብጽ ከ55 ቢሊዮን ኩዩቢክ በላይ የውሃ ድርሻን መስጠቱ ነው። ሱዳን የተሳተፈችበት የሁለተኛው ዙር ስምምነት የ18 ቢሊዮን ኪዩቢክ የውሃ መጠን የጋራ ሆኖ በታሪክ በአድሎ ይታወሳል። እኒህ ሁሉን አቀፍና የተፋሰስ ሀገራትን ግምት ውስጥ ያላስገቡ ስምምነቶች ዛሬም ድረስ ጥያቄ በመፍጠር አለመግባባትን በማወጅ እክል እየፈጠሩ ይገኛሉ።

እንግሊዝ ግብጽን ይዛ የመጀመሪያውን ዙር ስምምነት ስታደርግ የላይኛውን ተፋሰስ ሀገራት ማለትም ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ኡጋንዳን እና ኬንያን በመወከል ግን ደግሞ ሌሎች ሀገራትን ባላሳተፈ መልኩ ነበር። የሁለተኛው ዙር ስምምነትም ተመሳሳይ አዝማሚያ የነበረው በግብጽ ጥቅም ውስጥ የቅኝ ግዛት ፍላጎትን የማስፈጸም አይነት ተልዕኮ የነበረው እንደሆነ ለመረዳት ቀላል ነው። ይሄ ተልዕኮ ነው ዛሬም ድረስ ፍትህንና የጋራ ተጠቃሚነትን ወዲያ ብሎ የሶስትዮሽ ስምምነቱን እያደናቀፈ ያለው።

በዓባይ ወንዝ ላይም ሆነ በቀጣናው ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ኃያልነትና የተሰሚነት ሚና እንዴት ደበዘዘ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው የቅኝ ግዛት መስፋፋትን ተከትሎ የመጣው የአውሮፓውያን ጣልቃ ገብነትን ነው። በዓባይ ወንዝ ላይ የተደረጉትን ሁለት ኢ ፍትሐዊ ስምምነቶች የዚሁ እውነታ ማሳያ ናቸው። ስምምነቱ እንግሊዝ ግብጽን እንዴት በተደላደለ መንገድ መግዛት እንዳለባት ስታስብ የመጣ ራስን የመጥቀም ወይም ደግሞ ‹‹የእከክልኝ ልከክልህ›› አይነት ስምምነት ነው ።

> **በ**ዓባይ ወንዝ ላይም ሆነ በቀጣናው ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ኃያልነትና የተሰሚነት ሚና እንዴት ደበዘዘ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው የቅኝ ግዛት መስፋፋትን ተከትሎ የመጣው የአውሮፓውያን ጣልቃ ገብነትን ነው። በዓባይ ወንዝ ላይ የተደረጉትን ሁለት ኢ-ፍትሐዊ ስምምነቶች የዚሁ እውነታ ማሳያ ናቸው። ስምምነቱ እንግሊዝ ግብጽን እንዴት በተደላደለ መንገድ መግዛት እንዳለባት ስታስብ የመጣ ራስን የመጥቀም ወይም ደግሞ ‹‹የእከክልኝ ልከክልህ›› አይነት ስምምነት ነው

ይሄ የስምምነት ሸፍጥ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ በገዢና በተገዢ ሀገራት መካከል የተደረገ ጥቅምን የማስከበር የሴራ ጥንስስ ነው። እንግሊዝ በግብጽ፣ ግብጽ ደግሞ በዓባይ ላይ የበላይ እንዲሆኑ የተፈራረሙት አግላይ ስምምነት ነው። የዚህ ስምምነት አካል ሆነው ከተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው ከግብጽ መንግሥት ይሁንታ ውጪ የግብጽን ጥቅም የሚጎዳ ማንኛውም ተግባር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የሚደነግግ ነው ። ሌላኛው የስምምነት አካል ደግሞ ወንዙ ላይ የሚካሄድ የትኛውም የግድብ ግንባታ በግብጽ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዲሆን የሚያስገድድ ነው።

ሁለቱም የስምምነት መርሆዎች አሁን ላለው አስተሳሰብና ትውልድ የማይመጥኑ ከመሆናቸው በላይ በወንዙ ላይ ሰፊ ድርሻ ያላትን ሀገራችንን ያላቀፈ፣ ያላሳተፈ፣ ያስቆጣ ድርጊትም ነው። እንደዛ ባይሆን በገዛ መሬታችን፣ በገዛ ተፈጥሮ ሀብታችን ላይ በምንሰራው ግድብ ‹‹በርቱ፣ ጎበዙ›› ከማለት ባለፈ ማስፈራሪያና ዛቻ ባልደረሰብን ነበር። የሆነው ሆኖ ትውልዱ ዓባይን ገድቦታል። ከዚህ በኋላ የሚያስቆመው ምድራዊ ኃይል እንደማይኖርም ቃል በመግባት የተሰለፈ ነው።

የሦስትዮሽ ስምምነቱን አስመልክቶ ዛሬም ድረስ ላለው አለመግባባት በር ከፋች ሆነው ከፊት የሚመጡት እነዚያ ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችባቸው ስምምነቶች ናቸው። በግብጽ በኩል ድሮን እየጠቀሱ አልሸነፍ ባይነትን ማሳየት በእኛ በኩል ደግሞ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያንጸባርቁ ሃሳቦችን እያነሱ አብሮነትን ማስቀጠል ቢሆንም ስምምነቱን የሚያስታርቅ የጋራ መግባባት ላይ ግን አልተደረሰም። የመጀመሪያውን ጨምሮ ሁለተኛና ሦስተኛ አራተኛውም ዙር የሦስትዮሽ ስምምነትም በዚህ መልኩ ባለመግባባት የተቋጩ ናቸው።

ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበት ስምምነት ለዚህ አዲስ ትውልድ እና ለዚህ አዲስ ዘመን መከራከሪያ ሆኖ መነሳቱ አስቂኝ ቢሆንም ለዘመኑ በቀረበ አስታራቂ ሃሳቦች የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጡ ስምምነቶች እንደሚቋጭ እምነት አለን። ምክንያቱም ማንም የማይጎዳበት አብሮነትን የሚያጠነክር መነሻና መድረሻ የሃሳብ ስምምነት ስለሆነ ወደፊት የሚያራምደው። ተቃቅፎና ተደጋግፎ ከመልማት ውጪ አላማና ተልዕኮ እንደሌለን ጽኑ በሆነ የብዙሀነት ድምጽ በተደጋጋሚ የገለጽን ቢሆንም መጨው ገናናነታችን ያስፈራት ግብጽ ግን ከእምነታችን ጋር ለመቧደን አሻፈረኝ ስትል አስራ ሦስት ዓመታትን ተሻግራለች።

ያለፈውን ትተን ባሳለፍነው ዓመት ሐምሌ ወር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የግብጹ ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታህ አል ሲሲ ተገናኝተው የጋራ መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል። በዚህ የጋራ መግለጫ መሰረትም ላለፉት አራትና አምስት ወራት በህዳሴ ግድብ ዙሪያ የሦስትዮሽ ድርድር ሲካሄድ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን በማታውቀው ግብጽ በኩል ውጤት ማምጣት አልተቻለም። ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት የሚነሳው ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበትን ስምምነት እንደመከራከሪየ ማቅረቧ ነበር።

በፈረንጆቹ 2015 የጸደቀው የጋራ መርህ አብሮ መልማትን፣ አብሮ ማደግን፣ በፍትህና በእኩልነት መራመድን የሚደነግግ ቢሆንም ይሄ የጋራ መርህ ግን ከኢትዮጵያ በቀር ግብጾች ሲጠቀሙበት አይታይም። ለፈረሙበትና ላመኑበት መርህ ተገዢ መሆን አቅቷቸው ኢትዮጵያ ያልነበረችበትን በተንኮልና ሸር በውንብድናም የሆነውን የዛን ዘመን ስምምነት አስታውሰው የሚቀረሹ ሆነዋል።

ወደግድቡ አሁናዊ ሁኔታ ስንምጣ ፤ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት በተገኘ ወቅታዊ መረጃ መሰረት አጠቃላይ ሂደቱ 95 ከመቶ ያህል ተጠናቆ በመጨዎቹ ጥቂት ወራቶች ውስጥ ፍጻሜውን እንድናይ በሚያደርግ ንቃትና ብርታት ውስጥ ነው። የሲቪል ሥራ ግንባታው 98.9 ከመቶ ከመድረሱም በተጨማሪ ሁለት ተርባይኖቹ 540 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ላይ ይገኛሉ።

አሁናዊ የውሃ መጠኑ 42 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ሲሆን ሲጠናቀቅ ወደ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የሚደርስ የውሃ መጠን ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ 5150 ሜጋ ዋት የሚደርስ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መቻሉ ሌላ ብስራት ሆኖ የሚነሳ ነው። ሕዝባዊ እንቅስቃሴው እንደቀጠለ ነው ከሕዝብ በሕዝብ ለሕዝብ በሆነ መርህ በምንምነት ውስጥ እዚህ ደረጃ ስናደርሰው ብዙዎች በስላቅ አይችሉም፤ አይሆንላቸውም ሲሉን ነበር።

አለመቻልን ተረት አድርገን በራስ ገንዘብ፣ በራስ እውቀት፣ በራስ ጉልበት አንጸባራቂ ድልን አስመዝግበናል። በያዝነው የ2016 በጀት ዓመት በስድስት ወራት ሕዝባዊ ተሳትፎ ብቻ ከ643 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል። የግድቡ መሰረት ከተጣለበት ከመጋቢት 24/ 2003 ዓ.ም እስከ አሳለፍነው ወር ጥር መጀመሪያ ድረስ ከሀገር ውስጥና ከውጪ፣ ከቦንድ ሽያጭ፣ ከልገሳ ከተለያዩ ምንጮች ወደ 19 ቢሊዮን ብር ያህል ተሰብስቧል። ቀጣይ በሚኖረው ሂደትም መሰል ተሳትፎዎችን በማድረግ ፍጻሜውን ለማየት ብርቱ ርብርብ በመደረግ ላይ ነው።

ዓባይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የእውቀት፣ የጉልበት፣ የገንዘብና የጊዜ አሻራ ነው። መቀነትን ፈትቶ ያለንን ከመስጠት ጀምሮ የቻልነውን ሁሉ ያደረግንበት የህብረ ብሄራዊነት አርማችን ነው። ከድህነት ወጥተን፣ ከተረጂነትና ከኋላቀርነት ርቀን በኃይል ምንጭ ራሳችንን ከመቻል አልፈን ኢኮኖሚያችንን የምናሳድግበት አንዱ የተስፋችን መሰረት ነው። አጋምዶና አስተሳስሮ እናንተ ማለት ይሄን ናችሁ የሚል የአብሮነት መንፈስ የዘራብን ታሪካችን ነው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የደን ልማትን- ለአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ደን ለሰው ልጆችም ሆነ ለእንስሳት ህልውና እጅግ ወሳኝ ነው። የአፈር መከላት እና በረሃማነትን ለመከላከል፣የብዝሃ ሕይወት ሀብት ለመጠብቅ ፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የቱሪዝም መስህብ በመሆንም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በተለይ ዓለም አየር ንብረት ለውጥ እየፈተነ ያለበትን ሁኔታ ለማለፍ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው። የዓለም ሀገራት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት በሚያከናውኗቸው ተግባሮች ለደን ሀብት ልማት ትኩረት ሰጥተው በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ይስተዋላል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የደን ሽፋን 30 በመቶ ሲሆን ፤የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ደግሞ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ያህል ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በኩል ለደን ልማት በተሰጠው ልዩ ትኩረት በመርሀ ግብሩ የመጀመሪያ ምዕራፍ 25 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። በባለፈው ዓመት 2015 በጀት ዓመትም በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 7 ነጥብ 2 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። በተለይ የአምናውን ለየት የሚያደርገው ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ጭምር ችግኞችን በመስጠት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተምሳሌት የሚሆን ሥራዎችን እየሰራች መሆኑ ነው ።

የዓለም ሀገራት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያስችል ዘንድ ለደን ልማት ትኩረት ሰጥተው ይሰሩ ዘንድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ.ኤ.አ 2012 ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት የዓለም አቀፍ የደን ቀን በየዓመቱ ማርች 21 እንዲከበር ወስኗል። የዘንድሮ የዓለም የደን ቀን አከባበርም የደን ሀብቱን ማዘመን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በኢትዮጵያ በቅርቤ የተከበረው የደን ሀብት ልማትን ማዘመን በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በመምከር ነበር።

የዘንድሮ ዓለም አቀፍ የደን ቀን መሪ ቃል ከኢኖቬሽን ጋር የተገናኘ መሆኑ የቴክኖሎጂው ከደን ልማት አንጻር ያለውን ፋይዳና በምን መልኩ መጠቀም ይቻላል የሚለውን ለመገንዘብ ያስችላል ያሉት የኢትዮጵያ ደን ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሞቱማ ቶሌራ (ዶክተር) ናቸው።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የደን ሀብትን በዘመናዊ መንገድ በማስተዳደር አሁን ላለውም ሆነ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፈ ያስፈልጋል። ደን ውስጥ በርካታ የብዝሃ- ሕይወት ሀብቶች እና የገቢ ምንጫቸው በደን ላይ ያደረጉ ሕዝቦች አሉ። ደን ዓለም እየፈተነ ካለው የአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው። ይህም ሙቀት አማቂ ጋዞችን ከአየር ውስጥ በመምጠጥ እና ለሌሎች ዘርፎች ጭምር የተለያዩ የስነምህዳር ግልጋሎት በመስጠት ውጤታማና ምርታማ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

መጪው ትውልድ የተሻለ ምድር እንዲረከብ የደን መስፋፋትና መጠበቅ ብዝሃ ሕይወትን መጠበቅ ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ እንዲኖር እንደሚያደርግ ያመላክታሉ። ደን ካለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ መካከል አፈር እንዳይሸረሸር ፣የግብርናው ዘርፍ እና ከተሞች ውሃ ያለማቋረጥ እንዲያገኙ የሚያደርግ ከራሱ ዘርፍ በዘለለ ብዙ አበርክቶ ያለው መሆኑን አብራርተው፣ የደን ሀብትን ማልማትና መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል ።

ደን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለን መስተጋብር በመጨመር ለቀጣናው የኢኮኖሚ መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያም ደን ማልማት ላይ በርካታ ሥራዎችን እየሰራች መሆኗን ይገልጻሉ ።

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ በርካታ የተራቆቱ አካባቢዎች ይታያሉ። የእነዚህን አካባቢዎች ምርታማነት ለማሳደግ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች መተከል አለባቸው። እስካሁን በአረንጓዴ አሻራ በተሰራው ሥራ የተመዘገበው ውጤት ትልቅ ስኬት ያስገኘ ነው። እንደ አጠቃላይ አረንጓዴ አሻራ በደን ልማት የሚታይ ሲሆን፣ ያሉትን ደኖች መጠበቅ

> **ደን በሥርዓተ ምህዳር ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት እንደ ምሰሶ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የዝናብ ውሃን በመቆጣጠር፣ ውሃ ወደ መሬት እንዲሰርግና የአፈር ለምነት እንዲጠበቅ በማድረግ፣ ከባባዊ የአየር ንብረትን በመቆጣጠር ጭምር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት የሥርዓተ ምህዳር ሀብት ነው**

እና በደኑ ውስጥ ያሉትን ብዝሃ ሕይወት ሀብቶች እንዲጠበቁ ማድረግ የአረንጓዴ አሻራ አካል ነው።

የደን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች መስራታቸውን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ይጠቅሳሉ። ከተሰሩት ሥራዎች ውስጥ በአብዛኛው በአረንጓዴ አሻራ የተተከሉ ችግኞች እንደሚጠቀሱ ተናግረው፣ እነዚህ ችግኞች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ተናግረዋል፤ በተለይም ከ60 በመቶ በላይ የሚሆኑት ችግኞች በአርሶ አደሩ መሬት አካባቢ የሚተከሉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለምግብነት፣ ለእንስሳት መኖ የሚውሉ መሆናቸውን አመልክተዋል። አረንጓዴ አሻራ የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ለመቋቋም እና ያሉትን ደኖችና የብዝሃ ሕይወት ሀብቶች ለመጠበቅ በማለም የሚሰራ ማዕቀፍ ነው ሲሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በዘርፉ ብዙ ሥራዎችን እየሠራች ትገኛለች። እነዚህም ለመጪው ትውልድ የተሻለ አገርና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያመጡ የሚችሉ ከመሆናቸውም ባሻገር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ያሉትንም ደኖች መጠበቅን ያካትታል። በአሁኑ ወቅት የተፈጥሮ ደን እንክብካቤ ሥራ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየተሰራ ይገኛል።

‹‹የተተከሉ ችግኞች የጽድቀት መጠን መሻሻሎች የታዩበት ነው›› ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በባለፉት ጊዜያት ከተካሄደው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ብዙ ትምህርት በመውሰድ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። ዝርያዎችን ከአካባቢ ጋር የማመሳሰል እና ችግኞች ከሚተከሉበት አላማ ጋር በማስተሳሰር የሚሰሩ ሥራዎች መኖራቸውን እንዳሉና ይህም መሻሻሎችና ለውጦች እንዲታዩ አድርጎል ሲሉ አብራርተዋል።

ችግኞች እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የችግኞች የጽድቀት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል ሲሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። ቀደም ሲል የተተከሉት ችግኞች የጽድቀት መጠን ምን ይመስላል? የነበሩት ስኬቶች ምንድ ናቸው? የተገኙ ተሞክሮዎችስ ምን ይመስላሉ የሚሉትን የተመለከተ ጥናት ነጻ በሆነ ተቋም ተሰርቶ አልቆ እየተገመገመ መሆኑንም ጠቁመዋል።

‹‹ደን ለሰው ልጆች እንዲጠቅም ስለሚፈለግ ወደፊት በኢንዱስትሪ እየተመረተ ለሰው ልጆች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያስገኝ የሚችል ደን ሊኖረን ይችላል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ብዙ መልካም አጋጣሚዎች ስላሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ልክ እንደ አርሶ አደርና አርብቶ አደር እንደምንለው ሁሉ ‹ደን አደርን› መፍጠር ይቻላል›› ብለው እንደሚያስቡም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል። አሁን ላይ ደንን በማልማት የደን ሀብት መጠበቅና መንከባከብ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን እንዳለበት ያስገነዘባሉ።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ እያሱ ኤልያስ (ፕሮፌሰር) በበኩላቸው ደን በሥርዓተ ምህዳር ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት እንደ ምሰሶ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል መሆኑን ይገልጻሉ። የዝናብ ውሃን በመቆጣጠር፣ ውሃ ወደ መሬት እንዲሰርግ የአፈር ለምነት እንዲጠበቅ በማድረግ ከባባዊ የአየር ንብረት በመቆጣጠር ጭምር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት የሥርዓተ ምህዳር ሀብት ነው ይላሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ ይህ ሀብት ባለፉት ዘመናት ሲጨፈጨፍና ሲራቆት ቆይቷል። በዓመት እስከ 100 ሺ ሄክታር የተፈጥሮ ደን ሲመነጠር፣ በሰደድ እሳት ሲወድም ኖሯል። በዚህም የተነሳ ሀገሪቱ ለድርቅ፣ ለአካባቢ መራቆት፣ ለበረሃማነት፣ ለምግብ ጥረት እና ለድህነት ስትጋለጥ ቆይታለች። የድርቅ አለ ማለት ደግሞ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዳይኖር ያደርጋል። ዝናብ በሚከሰትበት ወቅት ደግሞ የዝናቡ ውሃ ሰርጎ ወደ ከርሰ ምድር ስለማይገባ ጎርፍ ሆኖ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። የአፈር መሸርሸር ይመጣል፤ የታችኛውን ተፋሰስ አካል ደግሞ ጎርፍ የሚያጠቃበት ሁኔታ ይከሰታል።

እንደ ሀገር ይህን ለመቀልበስና አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት አቅጣጫ ተቀምጦ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ያመላክታሉ። በዚህም የአረንጓዴ አሻራ ባለፉት አምስት ዓመታት በዓለም ትልቁ የአካባቢ ጥበቃ እና የደን ልማት ሥራ ተደርጎ ሊወሰድ በሚችል ደረጃ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ሃሳብ አመንጪነት በሕዝብ ተሳትፎ በርካታ ችግኞች የተተከሉበት ነው ብለዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በዚህ መርሀ ግብር 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን የተለያዩ ችግኞችን የተተኩሉ ሲሆን፤ 35 በመቶ ያህሉ የወደመውን የደን ሀብት የሚተኩ እና 60 በመቶ ያህሉ ለእንስሳት መኖ ፣ለፍራፍሬ እና ለተለያዩ የምርት አይነቶች የሚውሉ ችግኞች ናቸው።

‹‹በዚህም የደን መጨፍጨፍ ምጣኔን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ተችሏል›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ባለፉት ሃያ ዓመታት በአንድ መቶ ሺ ሄክታር መሬት ላይ ባለ የደን ሀብት ላይ ይደርስ የነበረውን ምንጣሮ አሁን ወደ 32 ሺ ሄክታር እንዲወርድ በማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል። በሌላ በኩል ለአርሶ አደሩ ማገዶ 58 ሚሊዮን ሜትሪክ ኪዮብ ደን እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ አርሶ አደሩ የሚጠቀመው ማገዶ ሲያጣ የሰብሎችን ተረፈ ምርቶች ለማገዶነትና ለእንስሳት መኖነት እንደሚጠቀም ያመላክታሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህ ሲሆን ደግሞ የአፈር ለምነት በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል። ይህን ለመከላከል በደን ልማት ላይ በትኩረት መስራት ስለሚጠይቅ አረንጓዴ አሻራ የደን ልማት የግብርና ቁልፍ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ‹‹ይህም ጎርፍን በመከላከል የአፈር ለምነት በማስጠበቅ፣ አማራጭ ማገዶ በማቅረብ የመሬቱን ጤንነትና ለምነት በማስጠበቅ፤ ምርትና ምርታማነት በመጨመር፤ ምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ራሳችንን እንድንችል የሚያስችል ቁልፍ ተግባር ነው›› ይላሉ።

በአካባቢ ጥበቃ የሚተከለውን ደን ብቻ ሳይሆን በአርሶ አደሩ የግል ማሳ ላይ ዛፎች እንዲተከሉ በማድረግ ዛፎች የውሃ ሚዛንንና የአፈር ለምነትን እንዲያስጠበቁ የሚደረግ መሆኑን አመላክተዋል። ከዚህ አንጻር የጥምር ደን እርሻ ጭምር በማስፋፋት የሀገሪቱን የደን ሽፋን 17 ነጥብ 2 በመቶ እንዲደርስና ዓመታዊ የደን ጭፍጨፋ ምጣኔ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ተደርጓል ሲሉም አስረድተዋል።

በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የሚለሙት የፍራፍሬ ተክሎች( አቦካዶ፣ ማንጎ...የመሳሰሉት) የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፈው ለውጭ ገበያ እየቀረቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ መርሀ ግብሩ የአቦካዶ ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሀገሪቱ ከአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃ ላኪ ሀገር እንድትሆን ማስቻሉን ተናግረዋል። በ2015 ጀምሮ በሌማት ቱሩፋት በጥምር ደን ላይ በተተከሉት ዛፎች እና በመኖ ተክሎች አካባቢ ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው የወተት፣ የማር እና የስጋ ምርት እንዲያመርቱ መደረጉን ገልጸዋል። ኅብረተሰቡ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ እና በሥርዓተ ምግቡ ላይ የተስተካከለ ሥርዓት እንዲኖር የሚያደርጉ ሰፊ ሥራዎች መሰራታቸውን አመላክተዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ በባለፈው ዓመት 6ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ፤ 7ነጥብ 2 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። ከአንድ ወር በፊት የቴክኒክ ቡድን በየክልሉ ተልኮ ባቀረበው ጥናት መሠረት ብሔራዊ አብይ ኮሚቴው ያረጋገጠው የችግኞቹ የጸድቀት መጠን 90 በመቶ ተመዝግቦል። የ2016 በጀት ዓመት እንደ አምና 6ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የመሬት ልየታ ተከናውኗል፤ እስካሁን 4ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች (በየጊዜው ችግኞች እየተዘጋጁ ስለሆነ ቁጥራቸው ከዚህም ሊጨምር ይችላል) ተዘጋጅተዋል ።

ከመጋቢት መጨረሻ እና ሚያዚያ መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ችግኝ ተከላ ይጀመራል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በልግ አብቃይና ዝናብ በሚያገኙ አካባቢዎች ዝግጅቱ መጠናቀቁን አስታውቀዋል፤ ዋናው የተከላ ሥራ በሰኔ ወር መጨረሻ በሀገራዊ የተከላ ፕሮግራም ይጀምራል ብለዋል። አሁን ላይ ችግኞቹ የሚተከሉባቸው ቦታዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጂኦግራፊካል መገኛቸውን በትክክል ለማወቅ የሚያስችል ሥራ ለመስራት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ እንደሆነ አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የሙአለ ሕፃናት ትምህርትና ሥነ-ዘዴው

ግርማ መንግሥቴ

ኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርትን ማስኬድ ከጀመረችባቸው የትምህርት ደረጃዎች አንዱ አፀደ-ሕፃናት (ኬጂ) መሆኑ ይታወቃል። በአሁኑ ዘመንም የትምህርት ደረጃው እንደሌሎቹ የትምህርት ደረጃዎች አስፈላጊው ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ እየተደረገ ላይ ይገኛል። በመላ ኢትዮጵያ ተግባራዊ እየተደረጉ ካሉት ሙአለ-ሕፃናት ተቋማት መካከል በመዲናዋ አዲስ አበባ የሚገኘውና በሞዴልነት ተወስዶ የብዙዎች አይን ማረፊያና የጉብኝት ምእራፍ የሆነው የአፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።

ሙአለ ሕፃናት (ኬጂ) ወይም የመጀመሪያው የልጅነት ትምህርት በመባል ይታወቃል። ለልጆች ትምህርት እድገትም አስፈላጊ አካል ሆኖ ይጠቀሳል። ልጆችን ለሁለት ዓመት በሙአለ ሕፃናት ፕሮግራም ማስመዝገብና ማስተማር የትምህርት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና የሕይወት ክህሎት ቀስመው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይረዳል። በአብዛኛውም የሶስት አመት ልጅ የመዋዕለ ሕፃናት ፕሮግራሞችን በየሳምንቱ ከ5 እስከ 15 ሰአታት እና የአራት ዓመት ሕፃናት ደግሞ ፕሮግራሞቹን ለ15 ሰአታት ይወስዳሉ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወደ ሙአለ ሕፃናት (ኬጂ) ፕሮግራም የሚገቡ ልጆች ቁጥሮችን መቁጠር፣ ቁጥሮችን እና ፊደሎችን መለየትና ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉና መሰል ክህሎቶችን ማዳበር ይጀምራሉ። በመዋዕለ ሕፃናት ልጆች በራስ መተማመንና ነፃነትን ይገነባሉ። ማህበራዊ ክህሎቶችን ይማራሉ። አዳዲስ ጓደኞችንም ያፈራሉ።

ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ሁለት ወይም ሶስት ዓመት የሙአለ ሕፃናት መርሀ ግብር የተከታተሉ ተማሪዎች በአስራ ስድስት ዓመታቸው በእንግሊዝኛና በሒሳብ ትምህርቶች ከሌላው የበለጠ ውጤት እንደሚያመጡ ጥናቶቹ ያመላክታሉ። እነዚህም "የተረጋገጡ ውጤቶች" ናቸው ይላል።



ፎቶ፦ ዳኜ አበራ

**ሞዴል የሆነው የአፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤት የአፀደ ሕፃናት ተማሪዎች፤**

ከመማር-ማስተማር ሥነዘዴ አኳያም ወላጆችና የሙአለ ሕፃናት አስተማሪዎች እንዴት አብረው መስራት እንዳለባቸው በጥናቱ ላይ የሰፈረ ሲሆን፣ ሙአለ ሕፃናት ወይም የሙአለ ሕፃናት ትምህርት በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች፣ ቤተሰቦች እና አስተማሪዎች መካከል አንድነት ተፈጥሮ በጋራ የሚከናወን ነው። የመማር-ማስተማር ስራውም በተሻለ ሁኔታ ይካሄዳል። ትምህርቱ ለልጆች እድገትና አጠቃላይ ሰብእና ግንባታም በጣም አስፈላጊ አካል ሆኖ ይወሰዳል።

በመሆኑም ወላጆች ወይም አሳዳጊ ትክክል የሆነውን ከስህተት፣ ቋንቋውን፣ ባህሉን እና እንደ ደግነትና መከባበር ያሉ እሴቶችን ለልጁ ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ቤተሰብ ስለልጁ ፍላጎት እና እንዴት መማር እንደሚፈልግ ማወቅ፤ መምህራንንም መጠየቅ አለበት። መምህራን በሙአለ ሕፃናት ላይ ስለሚሆነው ነገር እና ልጁ በቤት ውስጥ እንዴት መማር እንዳለበት ስለሚረዱ መንገዶች ይናገራሉ።

በሙአለ ሕፃናት ውስጥ አስተማሪዎች ልጆች በጨዋታ መልክ እንዲማሩ ያበረታታሉ። እነዚህም ሥዕል መሳል፣ መዘመር መዘመር፣ ተራራ መውጣት፣ መቆፈር እና ከቤት ውጪ መሮጥ፣ በአሻንጉሊት መጫወት እና መጽሐፍ ማንበብን ያካትታሉ። ጨዋታ ልጆች ከሌሎች ጋር በመተባበር ነገሮችን ሲጋሩ እና ተራ በተራ ሲጫወቱ፣ ሃሳባቸውን እንዲጠቀሙ እና አዲስ ነገሮችን እንዲያገኙ ያበረታታል። ልጆች ቋንቋን ለምሳሌ እንግሊዝኛን እንዴት እንደሚናገሩ እና እንደሚረዱ ጨምሮ ስለ ድምጾች፣ ቃላት እና ቋንቋ ይማራሉ።

የሙአለ ሕፃናት (ቅድመ ሙአለ ሕፃናት፣ ሙአለ ሕፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል) ተቋማትና ፕሮግራሞች ከሁሉም አስተዳደግ (ዳራ) የመጡ ወላጆችን የማህበረሰባቸው አካል በማድረግ በደስታ ይቀበላሉ። ወላጆች የሚገናኙበት፤ ታሪኮችን የሚለዋወጡበት እና እርስ በርስ የሚማሩባቸው ቦታዎች ናቸው። አስተማሪዎች ስለልጆችና ባህላቸው ማወቅ ይፈልጋሉ። ይህ ለልጆች ትርጉም ያላቸውን ፕሮግራሞች ያዘጋጁ ዘንድ ይረዳቸዋል። ይህም በባህላዊ ቀናት እና ዝግጅቶች ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎችንና በሌሎች ውስጥ ያለውን ልዩነት ማክበርን ያካትታል።

አስተማሪዎች ሁሉንም ልጆች በእንቅስቃሴዎች ውስጥ እኩል ያሳትፋሉ። ስለዚህ እንግሊዝኛ የማይናገሩ ልጆች እንደሌሎች የመጫወት እና የመማር እድሎችን ያገኛሉ ማለት ነው። አንዳንድ የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራሞች ትንሽ ቋንቋን ለምሳሌ እንግሊዝኛ የሚናገሩ ወይም ጭራሽ የማይናገሩ ልጆችን የሚረዱ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ አስተማሪዎች አሏቸው። እንዲሁም ልጆች ከሌሎች ጋር እንዲስማሙ፣ ሌሎችን እንዲቀበሉና የባህል ልዩነቶችን እንዲያከብሩ ያስተምሯቸዋል።

የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራሞች ዓይነቶችን በተመለከተም ልጆች የሦስት ዓመት ልጅ ሙአለ ሕፃናትን መርሀ ግብር በረዥም (ሙሉ) ቀን ማቆያ ማእከል ወይም ብቻውን የሚሰራ ሙአለ ሕፃናት መከታተል ይችላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ብዙውን ጊዜ ለአራት ዓመት ልጅ የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራም ይሰጣሉ።

እንዲሁም፣ የረጅም (ሙሉ) ቀን የእንክብካቤ ማዕከል የሙሉ ቀን ትምህርት እና እንክብካቤ መስጠት ይችላል። ይህም የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራምን ይጨምራል። በአስተማሪ የሚመራው የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራም ከተጨማሪ የትምህርትና እንክብካቤ ሰዓታትም ጋር ሊጣመር ይችላል።

ከአውስትራሊያ (Government of Victoria) የተገኘው ሰነድ የሙአለ ሕፃናት ፕሮግራም የሚሰራው በተወሰኑ ቀናትና በተወሰኑ ጊዜያት ብቻ መሆኑን ያሳያል። እራሱን ችሎ ለብቻው የሚሰራ አገልግሎት በዓመት በትምህርት ጊዜ ለ40 ሳምንታት የሚሠራ ሲሆን፤ ከትምህርት ቤቶች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ እረፍት ያደርጋል። እነዚህ ቀናት እና ሰዓታት የሚወሰኑት በሙአለ ሕፃናቱ በሚሰጡ አገልግሎቶች ነው ሲልም ነው የፕሮግራም አይነቶችን ከነምንነታቸው ነው ሰነዱ የሚያስረዳው።

ከቅድመ ሙአለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ሥርዓተ ትምህርትና ዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ቢሮ የሙአለ ሕፃናት መምሪያ መጽሐፍ እንደሚለው የሙአለ ሕፃናት ትምህርት ልጆችን በትምህርት ቤት እና በህይወት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ዝግጁ ያደረጋቸዋል። ሊያድጉና ሊማሩ የሚችሉበት አስተማማኝ ቦታ ነው። ወላጆችና መምህራን ስለልጆቹ የወደፊት ስኬታማነት ወሳኝ የሆነ ወዳጅነት የምጥሩበት ቦታ ነው። የማስተማር ፕሮግራሙ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ልጆች ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣምበት ቦታ ነው።

ከዚህ ባለፈ ሙአለ ሕፃናት ልጆች በማንበብ፣ በመፃፍ፣ በሂሳብ፣ በትላልቅ እና በትናንሽ የቡድን ትምህርቶች እና የትምህርት ማእከሎችን በመሳሰሉ፣ በተለያዩ የትምህርት ተሞክሮዎች የሚሳተፉበት ስፍራ ሲሆን፤ የልጆችን የማወቅና የአዲስ ግኝት ጉጉትና ደስታ ያበረታታል። ልጆች እንደ ልዩና ብርቅ ሰው ተቀባይነት የሚያገኙበት ስፍራም ነው። ራስን ማክበርና በራስ መተማመን የሚጠናከርበት ልዩ ቦታም ጭምር ነው።

እንደ የመማሪያ መጽሐፍ መረጃው ከሆነ ሙአለ ሕፃናት የራሱ ግቦችም ያሉት ሲሆን፤ እነዚም በራስ መተማመንን ማሳደግ፣ የመማር ዘይቤዎችን መከተልና፣ እውቀትና ክህሎትን ማዳበር ናቸው። በራስ መተማመንን በማሳደግ ግብ ውስጥ መከበርና ዋጋ መስጠት፤ ስኬትን መለማመድና ስሜትን በተገቢ ሁኔታ መግለፅን ያካትታል። የመማር ዘይቤዎችን መከተል በሚለው ግብ ስር ደግሞ መመርመርና አማራጭ መውሰድ፣ በግል፣ በጥንድ፣ ከብዙ እና ጥቂት ቡድኖች ጋር መስራት እና መጫወት፣ ሃሳብን እና አስተያየትን መግለፅና ችግሮችን በአግባቡ መፍታት ይካተቱበታል።

እውቀትና ክህሎትን ማዳበር በሚለው ግብ ስርም ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ ንግግር፣ እና መፃፍ፣ ዕቃዎችን መሰብሰብ፣ በትኩረት ማጤን፣ በስም መለየት፣ እና በአይነት እየለዩ መደርደር፣ መቁጠርና ማነፃፀር፣ ማወዳደር እና ከመጻሕፍትና ከተሞክሮዎች ታሪኮችንና ሃሳቦችን ማጋራት ይካተታሉ። እነዚህ በሌላው ዓለም የሚታዩ ቢሆንም ከሞላ ጎደል በአፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤትም ይታያሉ።

ለስደተኞች እና ለጥገኝነት ጠያቂ ሕፃናት ቀደም ብሎ ስለሚጀመር ሙአለ ሕፃናት (Early Start Kindergarten) ላይ "ሙአለ ሕፃናት መሄድ ለምን ያስፈልጋል?" በሚለው ንኡስ ርእስ ስር እንደ ሰፈረው ከሆነ፣ ሙአለ ሕፃናት፤ ልጆችን በትምህርት ቤት እና በህይወት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ዝግጁ ያደረጋቸዋል። በሙአለ ሕፃናት ውስጥ ልጆች ጨዋታን በመጠቀም ቋንቋን፣ ቁጥሮችን እና ቅርጾችን (ፓተርን) ይማራሉ። እንዲሁም ከሌሎች ጋር እንዴት መስማማት፣ መጋራት፣ ማዳመጥ እና ስሜታቸውን እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ ይረዳሉ። መምህራን ልጆች የማወቅ ጉጉት እንዲኖራቸው፣ ፈጠራን እንዲማሩ እና በልበ ሙሉነት እንዲማሩ ይረዷቸዋል።

ከቅድመ ሙአለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት እና ዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ቢሮ የሙአለ ሕፃናት መምሪያ መጽሐፍ" ከሙአለ ሕፃናት (Kindergarte) መማር ፕሮግራሞች አኳያም የልጆቹንና መምህራኑን ሚና አስፍሯል።

ልጆች በትላልቅ እና በአነስተኛ ቡድን መማር እና በአስተማሪዎች የሚመሩ ተሞክሮዎችን በሚያካትቱ የተለያዩ የመማር ክንውኖች ላይ እንደሚሳተፉ የሕፃናት መምሪያ መጽሐፉ ይጠቁማል። በዚህም በመዋእለ ህፃናት ቀን፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመጠቀም፣ ከሌሎች ልጆች ጋር ለመነጋገርና ለመጫወት፣ በጨዋታ ማእከሎችና በፕሮጀክቶች የተማሩትን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ እድሎች ይኖሯቸዋል።

የሙአለ ሕፃናት አስተማሪ እያንዳንዱ ልጅ ያገኘ(ች)ውን እውቀትና ክህሎቶች ለመሰነድ እንዲቻል እያንዳንዱን ለውጥና መሻሻል በጥንቃቄ እየተከታተለ(ች) ይመዘግባል/ትመዘግባለች። በተጨማሪ፣ የተማሪዎችን ችግር የመፍታት ችሎታ ለማዳበር፣ አስተማሪዎች ብዙ ቀልጣፋ ተግባራትን እያከናወኑ የመማር ልምምዶች ይሰጧቸዋል።

የወላጆችን የትምህርት ተቋማት ጉብኝት በተመለከተም «ትምህርት ቤቱንና የልጅዎን መማሪያ ክፍል እንድትጎበኙ እናበረታታለን። የጉብኝት ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ ለት/ቤቱ ይደውሉ። ሕንፃው ውስጥ እንደገቡ ወደ ትምህርት ቤቱ ጽህፈት ቤት ብቅ ብለው የጎብኝት ባጅ ማግኘት እንዳለብዎት ያስታውሱ» በማለት ወላጆች ከልጆቻቸው ትምህርት ቤት መራቅ እንደሌለባቸውና ስለልጆቻቸው ውሎና የወደፊት አቅጣጫ በአግባቡ መከታተል እንዳለባቸው ያሳስባል። ይህ ደግሞ ለሁሉም ሀገርና ለሁሉም ሙአለ ሕፃናት ይሰራል ብለን እናምናለንና በልጆች አስተዳደግ፣ አያያዝና የወደፊቱን የነቃ ትውልድ የመፍጠሩ ከባድ ሥራ የመምህራን ብቻ እንዳልሆነ ያመላክታል። ወላጆችም ከዚሁ አኳያ ሊንቀሳቀሱ ግድ ይሆናል ብለን እናምናለን።

የአፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር አቶ አክሊሉ እሸቱ እንደሚናገሩት፤ የወላጆች ክትትል የሚፈለገውን ያህል አይደለም። ነገር ግን አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ አንደኛ ደረጃ (ከኬጂ 1 እስከ ኬጂ 3)ን ወቅታዊ ይዘታ ስንመለከት የምናገኘው ዘመናዊነትን ሲሆን፣ መገለጫውም የኬጂ 1 ተማሪዎች በተሟላ ሁኔታ ትምህርታቸውን መከታተል መቻላቸውና ትምህርት ቤቱም በሞዴልነት ለሌሎች አርአያ ሆኖ መቅረቡ ነው።

አፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ መደበኛ ትምህርትንም የሚሰጥ ተቋም እንደ መሆኑ መጠን ጥራቱን የጠበቀ፤ ለሌሎች በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችል፤ ፅዳቱ የተሟላና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት ባሟላ መልኩ ሕፃናትን (ከኬጂ 1 እስከ ኬጂ 3) እያስተማረ ይገኛል።

ኬጂ 1 እና 2 ተማሪዎች ያማረ ምንጣፍ ላይ እንደፈለጋቸው፣ ተገቢ ባለሙያ ተመድቦላቸው እየተንከባለሉ የሚያነቡ፣ የሚጽፉና የሚጫወቱ መሆናቸው የተነገረንና እኛም የተመለከትን ሲሆን፤ ከምሳ በኋላም ለአንድ ሰዓት ያህል የእንቅልፍ ሰዓታቸውን የሚያሳልፉበት ያማረ መኝታ ክፍል ከተሟላ ፍራሽና ትራስ ጋር መሰናዳቱን ተመልክተናል። ይህም በራሱ ሌሎች ሊወስዱት የሚገባ ተሞክሮ መሆኑ በበርካታ የሥነትምህርት ባለሙያዎች ተመስክሮለታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ ጋር በመሆን የአፍሪካ ከንቲባዎች የሊደርሺፕ ኢኒሼቲቭ (AMALI) ተሳታፊዎችን አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ማስጎብኘታቸው ይታወሳል። ሰፊ የሚዲያ ሽፋንም አግኝቶ እንደነበር አይዘነጋም።

የጉብኝቱ አላማም "ጉብኝቱ በዋናነት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቀዳማይ ልጅነት ፕሮጀክት አተገባበር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በማየት ፕሮግራሙን በቀጣይነት ለመደገፍ እንዲቻል ታስቦ የተካሄደ" መሆኑ የተነገረ ሲሆን፤ የጉብኝቱ ተሳታፊዎችም" በትምህርት ቤቱ (አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ቅጥር ግቢ በመዘዋወር የሕፃናቱን የመማሪያ፣ የመጫወቻ እና የማሸለቢያ ክፍሎች" መጎብኘታቸው ታውቋል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ሀገራዊ የሆኑ ፕሮጀክቶች በዞናችው በመሠራት ላይ በመሆናችው ቀጣዩ ጊዜ ብዙ ተስፋ የሚሰነቅበት ነው››

*- አቶ ዳዊት ገበየሁ*
*የዳውሮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ*

አስቴር ኤልያስ

**የንጉስ ሃላላ ምድር ዳውሮ፣ በምዕራብ ደቡብ ክልል ከሚገኙ ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው። ዞኑ፣ በርከት ያለ የድንጋይ ከሰልን ጨምሮ ሌላ ማዕድን የሚገኝበት ሲሆን፣ በግብርናው ዘርፍ ደግሞ የተለያየ ምርት ለማምረት የሚያስችል ሰፊ መሬት ባለቤትም ነው። በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) አነሳሽነት የተሰራው “የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት” አካል የሆነው እና በንጉሥ ሀላላ ስም የተገነባው የሃላላ ኬላ ሪዞርት የሚገኘው በዚሁ ዞን ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ የቱሪስት ፍሰትንም እያስተናገደ ይገኛል።**

**ስለ ዞኑ አጠቃላይ ገጽታ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ልማትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በቅርቡ ወደስፍራው ባቀናበት ወቅት ከዳውሮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ከአቶ ዳዊት ገበየሁ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጓል። መልካም ንባብ።**



ፎቶ፡ ሀዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ዳውሮ በምዕራብ ኢትዮጵያ ከተካለሉ ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው፤ በአሁኑ ወቅት በዞኑ እየተካሔደ ስላለው እንቅስቃሴ ቢገልጹልን?**

**አቶ ዳዊት፡-** የዳውሮ ዞን ቅርብ ጊዜ ከተዋቀሩ የአዲሱ የደቡብ ምዕራብ ዞኖቹ መካከል አንዱ ነው። በዚህ መነሻ በዞኑ በርካታ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ እንዲሁም የኢኮኖሚ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከዚህ አንጻር ውጤቶችም በመመዝገብ ላይ ናቸው። የሕዝብ የመልማት ጥያቄዎች ከለውጡ ወዲህ ምላሽ እያገኙ በመሆናቸው በተሻለ ሒደት ላይ እንገኛለን።

እንደሚታወቀው ቀደም ባለው አወቃቀር ዞኑ የነበረው በደቡብ ክልል ውስጥ ነው። በዚያን ጊዜ የእኛን ዞን ጨምሮ ሌሎች ዞኖችም የአስፓልት መንገድ የሚባል አልነበራቸውም። ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ከለውጡ ወዲህ የተጀመሩ የአስፓልት መንገዶችን ማጤን ይቻላል። በወላይታ በኩል ያለው አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው። ከዚያም አልፎ በክላስተር የመደራጀት ጥያቄም መመለስ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህም ማሳያው እንደክልል ሲታይ የማኅበራዊ ክላስተር ያለው በዞናችን ውስጥ ነውና ይህም መልካም የሚባል አሰራር ነው።

በተለይ ደግሞ እኩል ከመልማት አንጻር የፍትሃዊነት ጥያቄዎች እየተመለሱልን ይገኛሉ። በርካታ ኢንቨስተሮችም ወደዞናችን እየገቡ ነው። በተለይም ሀገራዊ የሆኑ ፕሮጀክቶች በዞናችው በመሰራት ላይ በመሆናቸውም ቀጣዩ ጊዜ ብዙ ተስፋ የሚሰነቅበት ነው ለማለት እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከማህበራዊ ጉዳይ አኳያ ምን የተሰሩ ስራዎች አሉ?**

**አቶ ዳዊት፡-** ከማኅበራዊ ጉዳይ አኳያ አንዱ የማኅበራዊ ሴክተር ባህልና ቱሪዝም ነው። በአካባቢያችን በርካታ የቱሪስት መስህቦች አሉ። ከእነዚህ የቱሪስት መስህቦች ውስጥ ለአብነት ያህል ለመጥቀስ የሃላላ ኬላውን ጨምሮ የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ እንዲሁም ዋሾዎች፣ ፍል ውሃዎች፣ ፏፏቴዎችና ሌሎች ታዋቂ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማትም ጭምር የሚገኙበት ነው።

ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው የታላቁ ንጉስ ሃላላ ኬላ ሎጅ አንዱ ሲሆን፣ ይህም ሎጅ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ተመርቆ ወደሙሉ ትግበራ ውስጥ መግባት የቻለ ነው። እውነት ለመናገር ዞናችን በበጀት እጥረት ውስጥ በመሆኑ ትልቅ ቀውስ ውስጥ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ከሃላላ ሎጅ በየወሩ ከሁለት እስከ ሶስት ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ችለናል።

ይህንን ገቢ በዞናችን ውስጥ ያለው የሎማ ወረዳ የሚያገኘው ሲሆን፣ ዞኑ ለሎማ ወረዳ በየወሩ የሚያስተላልፈውን ወጪ የሚሰጠው በጀት ከሃላላ ኬላ ሎጅ የሚያገኘውን ገቢ በመቁረጥ ነው። ከዚህ የተነሳ የሎማ ወረዳ የነበረበትና በየወሩ የሚከፍለው እዳ እየተቀነሰ መምጣት ችሏል ማለት ነው።

እንደሚታወቀው የንጉስ ሃላላ ካብ የቆየ ነው፤ የድንጋይ ካብ ነው፤ እኛም ለዘመናት በአጠገቡ ስንመላለስ ቆይተናል። ይሁንና በወቅቱም ምንም አይነት ትርጉም አልሰጠነውም። ነገር ግን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አንድ ጊዜ በመጡበት አጋጣሚ ቦታውን ካስተዋሉ በኋላ ስፍራው ከዚያ ቀጥሎ የሆነው የቱሪስት መስህብ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከሃላላ ኬላ የገበታ ለሀገር አካል ሆኖ እስከ ዋካ ኢሰራ የአስፓልት መንገድ መስራት ጭምር ሊታቀድ ችሏል። በአሁኑ ወቅት ግምት ሁሉ የወጣለት ሲሆን፣ በቅርቡም ለመስራት የሚያስችል ሒደት ላይ ይገኛል። ስለዚህ እነዚህን መሰል ስራዎች ስናጤን ጉዳዩም ሆነ ሀብቱ ቀደም ሲል የነበረ፤ ነገር ግን እኛ ማጤን ያልቻልነው ነው። ስለዚህ በጠቅላይ ሚኒስትራችን አማካይነት እንደ ሀገር ታቅዶ የሚሠራ ታላቅ ሥራ ነው።

በእርግጥ ለዚህ ዓመት ብቻ የእፎይታ ጊዜ ተብሎ በአካባቢው ማለትም ሎጁን የሚያስተዳድሩ ባለሀብቶች የአንድ ዓመት ጊዜ ተሰጥቷቸዋል እንጂ ከዚህ በኋላ ለሚመጡት ዓመታት የተሻለ ገቢ ማግኘት ይቻላል ብዬ አስባለሁ።

ሌላው አስቀድሜ እንደጠቀስኩት የማኅበራዊ ክላስተር ያለው በዞናችን እንደመሆኑ የክልሉ ጤና ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ትምህርት ቢሮ ያለው በዞናችን ዋና ከተማ ተርጫ ነው።

ቀደም ሲል የተርጫ ከተማ አሁን የተላበሰውን አይነት ገጽታ አልነበረውም፤ በአሁኑ ወቅት በከተማችን በርካታ ለውጦች አሉ። በክልል ደረጃ ያሉ ቢሮዎችም ድጋፍ በማድረግ ላይ ናቸው። ከዚህ በኋላም ለተሻለ እድገት በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።

ከትምህርት ሴክተርም አንጻር ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አሉ። ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለው ተማሪ በአካባቢው (ዳውሮኛ) ቋንቋ መማር አለበት በሚል እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ለዚህም ስኬታማነት የመጽሐፍ ሕትመቶችን ለማከናወን ሕዝቡን በማነቃነቅ ላይ እንገኛለን። ከዚህ አኳያ ለዚህ የመጽሐፍ ሕትመት ሲባል ብቻ የራሱ አካውንት ተከፍቶ ገንዘብ እየተሰበሰበ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ጨረታው አልቆ ወደ ሕትመት ውስጥ የተገባበት ደረጃ ላይ መድረስ ተችሏል። እንዲያም ሆኖ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር በአግባቡ ሊሰራባቸው የተገቡ ጉዳዮች መኖራቸው ሳይዘነጋ ማለት ነው።

ለምሳሌ በተለይ ዩኒቨርሲቲ የመግባት ምጣኔው በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ጉድለቶች ላይ በደንብ መስራት አለብን ወደሚለው ድምዳሜ መጥተናል። በርካታ ተማሪዎችን ዩኒቨርሲቲ ማስገባት ነበረብን። አሁን ባለው ሁኔታ እንደ ሀገር ተይዞ እየተሰራ ያለው ሥራ በጣም ጥሩ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ትምህርት እንደ ሀገር ተወዳዳሪ የሆነን ዜጋ ከማፍራት አንጻር አጽንዖት ተሰጥቶት እየተሰራበት ያለ ሥራ በመሆኑ ትልቅ ጉዳይ ነው። እሱን እንዳንቃለን፤ በዚያ ልክ ግን እየሰራን ነን ወይ? ተማሪውን በጥራት እያፈራን ነን ወይ? የሚለው ነገር የእኛ የቤት ሥራ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ታችኛው ደረጃ ላይ መስራት ግድ ይላልና በአጸደ ሕፃናት አካባቢ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ዳዊት፡-** ጥያቄው ትክክልና ተገቢም ነው፤ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችም አሉ። በእርግጥ ከአጸደ ሕፃናት ጋር በተያያዘ ከተማ አካባቢ ብዙም ችግር የለውም። ከተማ አካባቢ የግል ትምህርት ቤቶች አሉ። ትምህርት መስጫ ማዕከላቱ በዞን ከተማም ሆነ በወረዳ ከተማዎችም ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ልምድ በገጠር ከተሞችም እየተስፋፋ ነው። መንግሥትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ስለሆነ በዛ ልክ በተለይ እስከ ስድስት ዓመት ላሉ ልጆች ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ ረገድ እየተሰራ ነው።

ተማሪዎች አንደኛ ክፍል እስከሚገቡ ድረስ በጣም ትኩረት ሰጥተን መስራት አለብን በሚል ታቅደው እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አሉ። እንዲያም ሆኖ ሰፊ ጉድለት እንዳለውም በመረዳታችን በቀጣይ ሰፊ ሥራ እንዳለብን አምነን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር አቀፍ በግብርናው ዘርፍ እየተሰራ ያለ በርከት ያለ ሥራ እንዳለ ይታወቃል፤ ከዚያ አኳያ እንደ ዞን በተለይ ከመስኖ ስንዴ ጋር ተያይዞ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ዳዊት፡-** እንደሚታወቀው የሀገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ግብርና ነው። ለሀገር ውስጥ ምርት እድገት (GDP) ያለው አስተዋጽኦም በጣም ከፍተኛ ነው። ለጊዜው እኛ ትኩረት አድርገን እየሰራን ያለነው በበጋ መስኖ ስንዴ እና በተፋሰስ ልማት ላይ ነው። ምናልባት አሁን ካለው ሁኔታ አንጻር የተለየ ቢሆንም፤ ቀደም ሲል ሃሳቡ ሲመጣ በ2015 ዓ.ም አሁን የበጋ ስንዴ የሚባለው “ስንዴ በበጋ እንዴት ይመረታል?!” የሚል እሳቤ ነበር።

ይህ ተነሳሽነት የጠቅላይ ሚኒስትራችን ነው። ይሁንና “እንዴት ይቻላል? እንዴትስ ይታሰባል?” የሚል አተያይ ነበር። ይህ አስተሳሰብ በእኛ በአመራሩም ውስጥ የነበረ ነው። እውነት ለመናገር ጉዳዩ ከገባን በኋላ የመጡ ለውጦች አሉ። በ2015 በጀት ዓመት ላይ የእኛ እቅድ አራት ሺ 152 ሔክታር መሬት ላይ ማልማት ነው።

ይህን የ2015 በጀት ዓመት ውጤት ካየን በኋላ ለ2016 ደግሞ እቅድ ይዘናል፤ ይኸውም ያቀድነው ወደ ሶስት ሺ 445 ሔክታር መሬታ ላይ ማልማት ነው። እስካሁን ድረስ ወደ 900 ሔክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። በእርግጥ ይህን ቁጥር ከእቅዱ አንጻር ስናየው ዝቅተኛ ነው። ይሁንና በፍጥነት እየተሰራ ይገኛል።

የግብርና ግብዓት ድጋፍን በሚመለከት የምርጥ ዘር አቅርቦት ወደ 296 ኩንታል ቀርቧል። ሌላውን ደግሞ ከአንዱ አርሶ አደር ወደሌላው አርሶ አደር በማዘዋወር ዘር እየተዘራ ይገኛል። እንደ ሀገርም የተያዘውን እቅድ ስናይ ከራሳችን ፍጆታ አልፈን ወደውጭ ሀገርም ኤክስፖርት ለማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ በዞናችን ጌና ወረዳ ያለውን የበጋ መስኖ ስንዴ ማየት ይቻላል። በዚያ አካባቢ በጥሩ ሁኔታ መንቀሳቀስ ችለናል ማለት ይቻላል።

ሌላው ተፋሰስ ላይ የሚሰራ ሥራ ሲሆን ይህም በዞን ደረጃ ንቅናቄ ተደርጎ እየሄድንበት ያለ ተግባር ነው። ወደ ሥራ የተገባውም ከአጠቃላይ ሕዝብም 33 በመቶ በተፋሰሱ ሥራ ይሳተፋል በሚል በመለየት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የመንገድ ዝርጋታ ፕሮጀክት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ዳዊት፡-** ትልቁ ነገር በአካባቢያችን የጸጥታ ችግር የሚባል ነገር አለመኖሩ ነው። ከዚህ አንጻር ቱሪስቶችን መሳብ ይቻላል። ለዚህም ደግሞ የቱሪስት መስህቦች አሉን። ነገር ግን ከመሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ ያለው ነገር ሲፈትነን ይስተዋላል። አንዱ ጥያቄያችን የመንገድ ችግር ነው። ለምሳሌ ከሃላላ ኬላ እስከ ዋካ ያለው አስፓልት የታቀደው በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ነው። ብዙ ነገሩ አልቋል። ከዚህ ውጪ ያሉትን ምን ማድረግ አለብን? የሚለው ነገር ለምሳሌ የማኅበራዊ ትስስር ገጽን ብንወስድ በእሱ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።

ማኅበራዊ ትስስር ገጽን በትክክል መጠቀም ከቻልን ጠቀሜታው በጣም ጉልህ ነው። በማኅበራዊ ትስስር ገጽ ቅስቀሳ ብቻ ሕዝቡ ገንዘብ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ሀገራዊ የሆኑ ፕሮጀክቶች በዞናቸው...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

አዋጥቶ በ2015 ዓ.ም 96 ኪሎ ሜትር መንገድ መስራት ተችሏል። ይህ ወደ ገንዘብ ሲቀየር ወደ 23 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር ነው። ለምሳሌ ዲሳ ወረዳ፣ ዛባ ወረዳ ቶጫ ወረዳ እንዲሁም ማልጋ ወረዳ ላይ የመንገድ ሥራ ተሰርቷል። በመንገድ ስራው የተሳተፈው ዳውሮ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሰው ብቻ አይደለም። ለአብነት ማንሳት ካስፈለገ ከውጭ ሀገር ለመንገድ ሥራ በሚል ገንዘብ የላኩ አሉ። የበጀት እጥረቱም ስላለ የመንግሥትን እጅ ብቻ የምንጠብቅ ከሆነ ጉዳዩን ከባድ ያደርገዋል በሚል በዚህ መልኩ ለመንቀሳቀስ ሞክረን ጥሩ ውጤትም አግኝተንበታል።

ይህ ሥራ በመንገድ ሥራ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ሳይሆን በጤናም ሆነ ትምህርት ቤት ግንባታ ላይ የሚንጸባረቅ ነው። ለምሳሌ ጌና ወረዳ ላይ እኔ ራሴ በማህበራዊ ትስስር ገጼ ላይ መነቃቃት እንዲፈጠር አድርጌያለሁ። በአሁኑ ወቅት በቦታው የትምህርት ቤት ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል። እንዲህ ሲባል ከመንግሥት ምንም አይነት ገንዘብ ሳናወጣ ማለት ነው።

ማሪ መንሳ ወረዳ ላይ ደግሞ ከሰሞኑን ቅስቀሳ ተደርጎ በርካታ ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ላይ ነው። ትልቁ ችግራችን የመንገድ ችግር ነው። ይህን ችግር ደግሞ መፍታት ያለብን ሕዝቡን በማስተባበር ነው።

በለውጡ ጊዜ ትልቁ ጥያቄ የነበረው የመንገድ ጥያቄ ነው። ይኸውም አንዱ በፌዴራል መንግሥት ምላሽ የተሰጠው እና ትልቁ ጥያቄ የነበረው ወልድሃኔ-ዱራሜ-ዱርጊ የሚባለው በጣም አጭር መንገድ አለ፤ እሱ መንገድ ጅማሬ ላይ ይገኛል። ይህ መንገድ አጭር ይሁን እንጂ ደቡብ ምዕራብን ከየትኛውም አካባቢ ማገናኘት የሚችል መንገድ ነው። የታርጫ-አሙናዳ መንገድ ደግሞ ሥራ ከጀመረ ቆየት ብሏል። የዱራሜ-ዱርጊ በዚያ በከንባታ በኩል ጥሩ እየተሰራ ይገኛል።

አምና ከፍ ያለ የመልካም አስተዳደር ችግር ነበር። ይህም መነሻው የታርጫ-ዋካ መንገድ ነው። መንገዱ በመዘጋቱ ወላዶች ሕይወታቸውን አጥተዋል። በአሁኑ ወቅት የተያዘው በፌዴራል መንግሥት ሲሆን፣ ግንባታውም በመጠናቀቅ ላይ ነው። በመሆኑም የመንገድ ችግሮች እየተፈቱ ናቸው ማለት ይቻላል።

ሕዝቡን በማነቃነቅ የተሰሩ ስራዎች አሉ። መንግሥትም በተመሳሳይ እየሰራው ያለ ነገር አለ። ከታርጫ ወደ ጭዳ የሚወስደው መንገድ አስፓልት ነበር። አጋጣሚ ሆኖ የመንገድ ስራውን የያዙ ኮንትራክተሮቹ ባለመቻላቸው እንደገና ጨረታ ወጥቶ ወደ ሥራ እየተገባ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ ትልቅ የመልካም አስተዳደር ችግር የታየበት ነው ተብሎ የሚጠቀሰው ከታርጫ ወደ ጅማ የሚወስደው መንገድ ነው። ወደ ዴዶ አካባቢ ደግሞ ጥሩ የሚባል ጅማሮ አለ ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ ምን ይመስላል? ለኢንቨስተሮች ምንስ ምቹ ሁኔታ አለ?**

**አቶ ዳዊት፡-** ኢንቨስትመንት ለኢኮኖሚ ያለው ፋይዳ ከግብርናው አይተናነስም ማለት ይቻላል። ኢንቨስትመንት ከሌለ እድገት የለም። ማደግ የሚባል ነገር አይታሰብም። ስለዚህ በገጠርም በከተማም ኢንቨስተሮችን መሳብ የግድ ነው።

በእኛ ዘንድ በከተማም ሆነ በገጠር ሰፊ የሆነ መሬት አለ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ኢንቨስተሮችም እየመጡ ናቸው።

እንደሚታወቀው ከአንድ ወረዳ አርሶ አደሩ የሚከፍለው ግብር አለ። ይህንን የክፍያ መጠን ግን አንድ ኢንቨስተር ብቻውን ይከፍለዋል። ስለዚህ ኢንቨስተሮችን መሳብ ብንችል እና ምቹ ሁኔታን ብናመቻች በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉ ሁሉም አርሶ አደሮች የሚከፍሉትን ግብር አንድ ኢንቨስተር መክፈል ይችላልና ፋይዳው ላቅ ያለ ነው።

በቅርቡ የጀማመርናቸው ስራዎች አሉ። እውነት ለመናገር ግን ኢንቨስተሩም እኛም ዘንድ ማነቆዎች አሉ። በአሁኑ ወቅት በገጠር ግብርና የተሳተፉና ሥራ ላይ ያሉ 32 ኢንቨስተሮች አሁን ሥራ ላይ ያሉ



ናቸው። ዘጠኝ ኢንቨስተሮች ደግሞ በከተማው ሥራ ላይ ናቸው። ስራው ያለው በተለያየ ደረጃ ላይ ነው። በውሉ መሰረት በአራትና አምስት ዓመት ሰርተው የማይጨርሱም አሉ። በጥቅሉ የከተማ እና የገጠሩን ኢንቨስተሮች ብናስተውል በሥራ ላይ ያሉ 41 ናቸው። በአብዛኛውም የተሰማሩበት የኢንቨስትመንት ዘርፍ ግንባታ፣ ጥምር ግብርና በተለይ በቡና እና በፍራፍሬ ዘርፍም ጭምር ነው። ሰሞኑን ከአሜሪካ የመጣች አንዲት ኢንቨስተር በአቦካዶ ላይ ብቻ ለመስራት ተዘጋጅታለች።

ይሁንና በስመ ኢንቨስተር የተቀመጡትንና ወደ ተግባር ያልገቡትን ገምግመናል። በዚህም መሰረት ስድስቱን ለይተን እንዲወጡ አድርገናል። እነዚህ አካላት መሬት ይወስዱና አጥረው የሚያስቀምጡ ናቸው። በመሆኑም አካሄዳቸውን ፈትሸን ገለል እንዲሉ አድርገናቸዋል። 41 ኢንቨስተሮች ናቸው ያልናቸውም እነዚህን ገምግመን ከለየን በኋላ ነው።

ከእነዚህ ውጪ አዲስ በቅርቡ ርክክብ የተደረገው ከሶስት ኢንቨስተሮች ጋር ነው። እነዚህ ሶስቱም ኢንቨስተሮች የሚሰሩት ገጠር ላይ ነው። ሌሎች ሶስት ኢንቨስተሮች ደግሞ በሒደት ላይ ይገኛሉ። የከተማው ደግሞ ዘጠኝ ተጨማሪ ፕሮጀክት ቀርቦ የመሬት ልየታ ላይ እንገኛለን። ከዚህ ውጪ ያለው ሌሎች ተጨማሪ ሶስት ኢንቨስተሮች እኛ ዘንድ ቀርበው የነበረ ሲሆን፣ ጉዳዩ በአሁኑ ወቅት ለክልል እንዲቀርብ ተደርጓል።

ሌላው ኢንቨስተሮች አካባቢ ያለውን ችግር ለመወያየት ሞክረናል። ጥቂት የማይባሉ መሬት ይወስዳሉ። ያለባቸው ችግር በጊዜ አልምተው አለመጨረስ ነው። ለምሳሌ አንድ ሺ ሔክታር መሬት ከወሰዱ “ሁለት እና ሶስት መቶ ሔክታር መሬት አልምቻለሁ፤ ሌላው ምቹ አይደለምና ተለዋጭ ይሰጠኝ” የሚሉ ሰበቦች ይበዛሉ። መሬት ከወሰዱ በኋላ ሶስት እና አራት ዓመት ቆይተው ምዝገባ የማያካሔዱ እንዲሁም የሥራ ግብር ሁሉ የማይከፍሉ አሉ። አንድ ኢንቨስተር መሬት ወስዶ አራት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ምርቱ ማዕከላዊ ገበያ መቅረብ ይጠበቅበት ነበር። ነገር ግን እዚህ ላይ ክፍተት መግለጽ እወደዳለሁ። ቀስ አድርገው ለመውጣት የሚፈልጉትን ሰብሰብ አድርገን የመምከር እና የማስተካከል ሥራ መስራት ካልሆነ እግር በእግር ማሳደዱ ጠቀሜታ የለውም በሚል እየሰራን እንገኛለን።

ከዚህ በተቃራኒ በጥሩ ሁኔታ እያለሙ ያሉ

**ማኅበራዊ ትስስር ገጽን በትክክል መጠቀም ከቻልን ጠቀሜታው በጣም ጉልህ ነው። በማኅበራዊ ትስስር ገጽ ቅስቀሳ ብቻ ሕዝቡ ገንዘብ አዋጥቶ በ2015 ዓ.ም 96 ኪሎ ሜትር መንገድ መስራት ተችሏል። ይህ ወደ ገንዘብ ሲቀየር ወደ 23 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር ነው**

ኢንቨስተሮች አሉ። ለምሳሌ ዲሳ፣ ጌሰራ ወረዳን መጥቀስ ይቻላል። በተመሳሳይ ተርጫ ዙሪያም እንዲሁ ተጠቃሽ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዞኑ ያለው የማዕድን ሀብት ምንድን ነው?**

**አቶ ዳዊት፡-** በዞናችን የድንጋይ ከሰል ሀብት አለ። እኛ የምንከተለው መርህ ውጭ ሀገር የሚመረቱ ምርቶች በእኛ ሀገር ተመርተው እንዲተኩ ነው። ከዚህ አኳያ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ከመቀነስ አንጻር ፋይዳው የላቀ ነው። በተለይ ከደቡብ አፍሪካ በከፍተኛ ወጪ የሚመጣውን የታጠበ የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ከማልማት አንጻር በሚል ታቅዶ እየተሰራ ነው።

ለምሳሌ በዞናችን የሚገኘው የኢቲ ማዕድን ልማት ካፒታሉ ወደ አምስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ነው። እስካሁን ባለው ሁኔታ የፈጀው ወደ አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ነው። ጠቀሜታው ምንድን ነው የሚለው ሲፈተሽ የዚህ ፋብሪካ ሥራ በአንድ ወቅት 420 ጊዜያዊ እና ቋሚ ሰራተኛ ማሰራት ነበር። ጊዜያዊ ሆኖ ስራዎች ሲቆሙ መጨመር እና መቀነስ ሊታይበት ይችላሉ። በመሆኑም የሥራ እድል ከመፍጠር አንጻር ግን ፋይዳው ከፍ ያለ ነው። ፋብሪካው ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ 400 ቋሚ ሰራተኞችን የሚፈልግ ይሆናል። በሂደት ደግሞ በርካታ ወጣቶች የሥራ እድል የሚያገኙ ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

በሌላ በኩል ደግሞ እንደዞን በተለይ ትኩረት እንዲደረግልን የምንፈልገው በገጠር ግብርና ላይ ነው። ምክንያቱም በዞናችን ያልተነካ ሰፊ መሬት አለ። ስለዚህ ባለሀብቶች ፍራፍሬ፣ አትክልትና መሰል ነገር ላይ ቢያመርቱ እነርሱም እኛም ተጠቃሚ እንሆናለን። ቦታውም ተርጫ ዙሪያ በመሆኑ ቅርብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችውን ስምምነት በተመለከተ እርስዎ እንደ አንድ የዞን አስተዳዳሪ እና ኢትዮጵያዊ ያለዎ አተያይ ምን ይመስላል?**

**አቶ ዳዊት፡-** እኛ ኢትዮጵያውያን ከዛሬ 30 ዓመት በፊት የባህር በር የነበረን ነን። ያጣነው ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ነው። በአሁኑ ወቅት የሀገራችን መንግሥት ወደዚህ ውሳኔ ሲገባ ብዙዎቻችን “እንዴት ይሆናል?” በሚል ውዥንብር ውስጥ ገብተን እንደነበር የሚታወስ ነው።

በብዙዎችም ዘንድ አንዳች የሚፈጠር መጥፎ ነገር እንዳለም ስጋት እንደነበር የሚታወቅ ቢሆንም፤ ያለ አንዳች ኮሽታ ነገሮች መስመር ይዘው ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር የባህር በር ልታገኝ የሚያስችላትን ሰነድ መፈራረም ችላለች። ይህ ትልቅ ነገር ነው። ኢትዮጵም የተከተለችው ሰላማዊ የሆነ መንገድን ነው። በወቅቱ የስምምነት ሰነድ በተፈረመበት ጊዜ በዞናችን በየወረዳው እና በተለይ ተርጫ ከተማ ላይ ሕዝቡ ለደስታ መግለጫ የድጋፍ ሰልፍ በዕለቱ ወጥቶ ወደቤቱ የገባው ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ ነው። ይህ የሚያሳየው በሕዝቡ ዘንድ ላቅ ያለ ፍላጎት መኖሩን ነው።

ፈጣሪ ፈቅዶ ይህ የባህር በር በእጃችን እንዲገባ እንሻለን፤ ለዚህ ደግሞ የሚከፈል የትኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁዎች ነን። የባህር በር ተጠቃሚ መሆን ከጀመርን ደግሞ አሁን ካለንበት በላይ በኢኮኖሚያችን ለማደግ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርልናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ዳዊት፡-** የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየሰራ ያለውን ሥራ አደንቃለሁ። በራሳችሁ በጎ ፈቃድ በዞኑ ተንቀሳቅሳችሁ ለመጎብኘት ስለመጣችሁ በራሴና በዞኑ ነዋሪዎች ስም እጅግ አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የቆዳ ውጤት የእጅ ቦርሳዎች

**ሰሚራ በርሀ**

ሀገራችን በቆዳ ሀብቷ በእጅጉ ትታወቃለች፡፡ ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ ከምታቀርባቸው ምርቶች ውስጥ እነዚሁ የቆዳ ውጤት ምርቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የቆዳ ውጤቶቹ በሌሎች ሀገሮች ዜጎች ዘንድ በእጅጉ ተወዳጅ እና ተፈላጊ ናቸው ፡፡

ከእነዚህ የቆዳ ውጤቶች ውስጥ ለተለያየ አገልግሎት የሚውለው ቦርሳ አንዱ ነው፡፡ በአብዛኛው ሴቶች በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ቦርሳን የሚጠቀሙ ሲሆን፤ ወንዶችም አነስ ባሉ እና በተለምዶ ዋሌት የሚባለውን የኪስ ቦርሳ ይጠቀማሉ ፤ ከዛ በዘለለም የቆዳ ውጤቱ በተለያየ ዲዛይን እና መጠን በገበያ ላይ ይቀርባል፡፡

ወጣት ዮሐንስ በቀለ የቆዳ ውጤቶችን ተጠቅሞ ከእደ ጥበብ ጋር የተገናኙ ቦርሳዎችን እየሰራ ለሀገር ውስጥ እንዲሁም ለውጭ ገበያ ያቀርባል፡፡ ዮሐንስ ሙያውን በቴክኒክና ሙያ ከሚሰጠው የሌዘር ኢንስቲትዩት በመማር ያገኘ ሲሆን፣ ከዚያ በመቀጠልም ሌሎች ስልጠናዎችን በመውሰድ ይበልጥ ወደ ሙያው መዝለቅ ችሏል ፡፡ በአሁኑ ወቅትም በስሩ 11 ሰራተኞችን ቀጥሮ እየሰራ ሲሆን፣ በስራው ላይም ስድስት ዓመትን አስቆጥሯል ፡፡

‹‹ እኔ ተምሬ በወጣሁበት ሰዓት የቆዳ ውጤት ቦርሳዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች እንደአሁኑ ብዙ አልነበሩም፤ በማምረት ደረጃም የነበረው የሥራ እድል ጠባብ ነበር፡፡ አሁን ብዙ አምራቾች እና ኢንተርፕራይዞች ተፈጥረዋል፡፡›› የሚለው ዮሐንስ፣ አሁን ሰዎች በየጊዜው የሚወጡ ፋሽኖችን እንደየምርጫቸው በመከተል የቆዳ ውጤቱን ይጠቀማሉ፤ ለቆዳ ውጤቱ ያለው ፍላጎትም እየጨመረ መጥቷል ሲል ያብራራል፡፡ ዮሐንስ ሥራ ፈጣሪም ዲዛይነርም መሆኑን ጠቅሶ፤ የራሱ ዲዛይን እና ፈጠራ የሆኑ ከቆዳ የተሰሩ ቦርሳዎችን ለገበያ እንደሚያቀርብ ይገልጻል፤ የራሳቸውን ዲዛይን ይዘው ለሚመጡ ተቋማትም ሆነ በግል ለሚመጡ ደንበኞች እንደየምርጫቸው ይሰራል ፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው ሁኔታ ሰዎች የቆዳ ውጤት ቦርሳዎችን የሚመርጡት ከጥንካሬ እና ለረጅም ጊዜ



ከማገልገል አኳያ ነበር የሚለው ዮሐንስ፣ ገበያ ላይ የሚቀርበውን ይህን ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆኑን ገልጿል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያ ሁኔታ መቀየሩን ገልጿል፡ ፡ አሁን ለእለት ተዕለት ከሚያዙ ቦርሳዎች እጅግ ውድ እስከሚባሉት የጉዞ ቦርሳዎች ድረስ በገበያው ላይ ይገኛሉ ብሏል፡፡

እሱ እንዳብራራው፤ ከቆዳ ውጤቶች ለሚሰሩ ቦርሳዎች ዋናው ግብዓት ራሱ ቆዳው ነው ፡፡ ይህን የቆዳ ግብዓት በሀገራችን ካሉ የተለያዩ የቆዳ አምራች ፋብሪካዎች ለሀገር ውስጥ አምራቾች በሚደረገው አቅርቦት መሰረት በፋብሪካ ሂደት ያለፈን ቆዳ በሚፈልገው መጠን እና አይነት ይገዛል፡ ፡ የሚጠቀማቸው የቆዳ አይነቶች በአብዛኛው የበሬ ቆዳዎች ናቸው፤ በፋብሪካ ሂደት ሲያልፍ ደግሞ በአዞ ቆዳ ላይ ያለ የተለየ ቅርጽ እንዲኖረው ተደርጎ የሚዘጋጅ፣ ቀለም ያልተነከረ ቆዳን ይጠቀማል ፡፡

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ እንደ ችግር የሚነሳው የተለያዩ የግብዓት እጥረቶች ናቸው፤ እንደ ዮሐንስ ገለጻ፤ አሁን ይህ ችግር እየተቀረፈ ነው፤ በየጊዜው የሚኖረው የዋጋ መለዋወጥ እና አንዳንድ በደንበኞች ትእዛዝ የሚመጡ ለየት ያሉ ዲዛይኖች ያላቸው ቦርሳዎችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማግኘት ከመቸገር በስተቀር አሁን ያለው አቅርቦት ጥሩ ነው ፡፡

ከዚህ ቀደም የቆዳ ውጤት ቦርሳ ተጠቃሚዎች የነበራቸው የቀለም ምርጫ ጥቁር እና ቡኒ የቀለም አይነት እንደነበር የሚያስታውሰው ዮሐንስ፤ አሁን ግን በተለያየ የቀለም አማራጭ ሰዎች የቆዳ ውጤት ቦርሳዎችን ምርጫቸው እያደረጉ መሆናቸውን አስታውቋል፡፡ በአብዛኛው ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የቆዳ ውጤት ቦርሳን ምርጫቸው ያደርጋሉ ሲል ይገልጻል፡፡

ዮሐንስ የሚፈልገውን የቆዳ አይነት ከፋብሪካው በሚፈልገው መጠን ከተረከበ በኋላ ዲዛይነሩ ባዘጋጀው ንድፍ መሰረት ቆዳው ይቆረጣል ፤ ከተቆረጠ በኋላም በዲዛይኑ መሰረት ተሰፍቶ የማጠናቀቂያ ሥራ ከተሰራለት በኋላ በሚፈለው መንገድ ታሽጎ ለገበያ ይቀርባል ፡፡ ይህ ሥራ ከንድፉ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ውጤቱ ድረስ የእጅ ውጤት ሲሆን፤ እንደ ግብዓት የሚጠቀሙት ቆዳ የፍየል እና የበግ ከሆነ የመሳሳት ባህሪ ስላለው በእጅ ፣ የበሬ ቆዳ ከሆነ ደግሞ ማሽኖችን በመጠቀም ይቆረጣል፡፡ ቆዳው ተቆርጦ በሚሰራበት ጊዜ የሚተርፈውን ቆዳም የተለያዩ ዲዛይኖችን በማውጣት ቦርሳዎችን ያዘጋጃል፡፡

እነዚህ የቆዳ ውጤት ቦርሳዎች በገበያው ላይ ከፍተኛ ዋጋ ተተምኖላቸው የሚሸጡ ቢሆንም፣ ዮሐንስ ግን ለውጭ ገበያ ከሚያቀርው በተጨማሪ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላለው ማህበረሰብ ጭምር ምርቶቹን ያቀርባል፡፡

ዮሐንስ የተለያዩ ደንበኞች አሉት፤ በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች እና ባዛሮች ላይ ይሳተፋል፡፡ ከሀገር ውስጥ ባለፈ የሌሎች ሀገር ዜጎች የሚሳተፉባቸው ዓለምአቀፍ ባዛሮች ላይም ይሳተፋል፤ በእዚህ መድረክም የራሱ ዲዛይኖች የሆኑ ቦርሳዎችንና ሌሎች የቆዳ ውጤቶችን ይዞ ይቀርባል፡፡ በዚህም ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ደንበኞችን ያፈራበታል ፡፡

‹‹ የቆዳ ውጤት ቦርሳዎችን ብቻ የሚጠቀሙ ደንበኞች አሉኝ፡፡ በየስድስት ወሩ እየመጡ የተለያዩ ዲዛይኖችን የሚጠቀሙ ደንበኞችም አሉኝ ›› የሚለው ዮሐንስ፣ የቆዳ ውጤት ለሆኑ ቦርሳዎች ልዩ ፍቅር ያላቸው ደንበኞች እንዳሉትም አንስቷል ፡፡

የቆዳ ውጤት ቦርሳዎች ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ ቢሆኑም፣ ፋሽናቸውም በየወቅቱ ይለዋወጣል ፡፡ በአሁኑ ሰዓት ለመያዝ ምቹ የሆኑ ትንንሽ ቦርሳዎች ይፈለጋሉ፡፡ እሱ እና የሥራ ባልበደረቦቹ የገና በዓል እና የአውሮፓውያኑ አዲስ አመት በሚሆንበት ጊዜ ሥራ እንደሚበዛባቸው ይገለጻል ፡፡ በገና በዓል ሰዎች ስጦታ የመስጠት ልምድ እንዳላቸው ጠቅሶ፣ ለእዚህ ደግሞ ከቆዳ የተሰራ ቦርሳ ለስጦታ ምርጫቸው ያደርጋሉ ብሏል ፡፡

የተጠቀመውን ቆዳ ባህሪ ለደንበኞቹ በመንገር፣ አንድ የቆዳ ቦርሳን ምርጫው ያደረገ ሰው ቦርሳውን ውሀ ላይ እንዳያስቀምጥ ምክር እንደሚሰጥ ይገልጻል፡፡

ቦርሳዎቹ ከቆዳ የሚሰሩ እና የእጅ ውጤቶች እንደመሆናቸው የሚኖራቸው ዋጋም ከሌላው ይለያል ሲል የገለጸው ዩሀንስ ፣ ዋጋቸው እንደ ዲዛይኑ ፣ እንደሚፈጀው የቆዳ ውጤት እና እንደሚጠቀማቸው አንዳንድ ግብዓቶች ፣ ሰርቶ ለማጠናቀቅ እንደሚወስደው ጊዜ እንደሚወሰንም ተናግሯል፡፡ ፡፡ ቀለል ያሉ ቦርሳዎች ከአንድ ሺህ 500 ብር ጀምሮ ፣የሴት ቦርሳዎች እስከ አራት ሺህ ብር ድረስ ለገበያ እንደሚቀርቡም ጠቁሟል፡፡ ወንዶች በብዛት ለሚጠቀሟቸው ተንቀሳቃሽ ኮምፒውተሮች ( ላፕቶፕ ) የሚያገለግሉ ቦርሳዎች እስከ ስምንት ሺህ ብር ድረስ ፣ ለጉዞ የሚሆኑ ቦርሳዎች ደግሞ እስከ 15 ሺህ ብር ድረስ በገበያው ላይ ይገኛሉ ብሏል ፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ልማት… ሀብት ሳይባክን …

**አስናቀ ፀጋዬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ መንግሥት ‹‹የኮሪደር ልማት ብሎ›› በሰየመው ፕሮጀክት በከተማዋ የሚገኙ ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎችንና የእግረኛ መንገዶችን የማስፋት ሥራ በስፋት እያከናወነ ይገኛል። በዚህ ልማት ከፒያሳ መገናኛ፣ ከፍላሚንጎ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ መገናኛ፣ ከሜክሲኮ ሳር ቤት፣ ከመገናኛ ሃያት አደባባይና ሌሎችም አካባቢዎች ያሉ የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገዶች ፈርሰው እንዲሰፉ እየተደረገ ነው።

በዚህ የተሽከርካሪዎችና የእግረኛ መንገዶችን የማስፋት ሂደት በመንገድ ዳርቻ ያሉ ያረጁ ቤቶች፣ ሕንፃዎች፣ ዛፎች፣ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ እንጨቶችና ሌሎችም እንዲነሱ ተደርገዋል፤ አሁንም እየተነሱ ነው። መንገዶችን ለግንባታ ሥራ በማፅዳት እንቅስቃሴ የሥልክና የመብራት፣ የውሃና ፍሳሽና የመንገድ ገንቢ ተቋማት ቅንጅታዊ ሥራ ከዚህ ቀደም ከነበረው የተሻለ ሆኖ ታይቷል።

በመንገድ ዳርቻ የነበሩ ነዋሪዎች፣ የሕንፃ ባለቤቶች፣ የግልና የመንግሥት ተቋማት፣የእምነት ተቋማትና ሌሎችም ለልማቱ ያሳዩት ትብብርም እጅግ የሚደነቅ ነው። መንገዱን የማስፋት ሥራ በአጭር ጊዜ አጠናቆ ለተሽከርካሪና ለእግረኞች ክፍት ለማድረግ በመንግሥት በኩል ሌት ተቀን እየተደረገ ያለው ጥረትም ይበል ያሰኛል። ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ በርከት ያሉ ባለሙያዎች በፈረቃዎች ሌትም፤ ቀንም የግንባታ ሥራውን እያከናወኑ ይገኛሉ። ይህም በኢትዮጵያ የሥራ ባህል እየዳበረና እያደገ መምጣቱን ጠቋሚ ነው።

የኮሪደር ልማቱ ትችትም ወቀሳም ቀርቦበታል። ልማቱ ትችትም ወቀሳም ይቅረብበት ቁጥሩ እያደገ ለመጣው ሕዝብና ተሽከርካሪ ግን እጅግ አስፈላጊ የሆነና ለነገ የሚተውት ተግባር አይደለም። ዛሬ ላይ ጨክኖ ልማቱን ማስጀመር ካልተቻለ ነገ ከነገ ወዲያ እየጨመረ ከሚመጣው የግንባታ ዋጋ ጋር መጋፈጥ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ለልማቱ የሰፋ ጊዜ በተሰጠ ቁጥር የነዋሪው ችግር የዛኑ ያህል እያየለ ይሄዳል እንጂ ፈጽሞ አይቀንስም። ስለዚህ ዛሬን ጨክኖ ሰርቶና ትንሽ ተሰቃይቶ ነገን እፎይ ማለት ይሻላል።

የኮሪደር ልማቱ የከተማዋን ገፅታ ከመቀየር አንፃርም ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የማይታበል ሀቅ ነው። የከተማዋ ገፅታ ተቀየረ ማለት ደግሞ ለቱሪስት መዳረሻ ምቹ ስለሚያደርጋት ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ከማሳደግ አንፃር ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በመንገዶች ዳርቻ የተለያዩ መናፈሻዎችና ፓርኮች መገንባታቸው አይቀሬ ነው። ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎችም እንደሚሰሩ ጥርጥር የለውም። በዚህ የግንባታ ሂደትም ለበርካታ ዜጎች ቋሚና ጊዜዊ የሥራ እድል መፈጠሩ አይቀርም። ይህም የኮሪደር ልማቱን ሌላኛው ትሩፋት ያደርገዋል።

በዚህ ኮሪደር ልማት የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገዶች ስለሚሰፉ ለተሽከርካሪዎች የተሳለጠ ፍሰት እንዲኖር ያስችላል። በተመሳሳይ ለእግረኞችም ሳይገፋፉ በነፃነት መንገዶችን ለመጠቀም ያግዛቸዋል። መንገዱ በሰፋ ቁጥር የትራፊክ ምልልሱም የዛኑ ያህል ስለሚፋጠን የሰዎችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴን ያፋጥናል። ንግዱንም፤ ግብይቱንም ያሳልጣል። በዚህ ደረጃ መንገዶቹን ማስፋቱ በቀጣዮቹ ሃያና ሰላሳ ዓመታት እየጨመረ የሚመጣውን የሕዝብና

> **የኮሪደር ልማቱ በበጎ የሚታይና የሚደገፍ ቢሆንም ታዲያ ልማቱን በማካሄድ ሂደት የሚታዩ ስህተቶችን መጠቆም ደግሞ እንደ አንድ ዜጋ የግድ ይሳል**

የተሽከርካሪዎች ቁጥር ተሸክሞ ለማስተናገድ ጭምር ያግዛል።

የኮሪደር ልማቱ በበጎ የሚታይና የሚደገፍ ቢሆንም ታዲያ ልማቱን በማካሄድ ሂደት የሚታዩ ስህተቶችን መጠቆም ደግሞ እንደ አንድ ዜጋ የግድ ይላል። በዚህ ልማት በስፋት እየታየ ያለው ችግር የሀብት ብክነት ነው። የግንባታ ግብአቶች ምን ያህል እየተወደዱ እንደመጡ ሁሉም የሚመሰክረው ሀቅ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የመንገድ ጠርዞች እንደ አዲስ ተሰርተው የሚፈርሱበት ሁኔታ ይታያል። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ የኮሪደር ልማቱ እንደሚካሄድ እየታወቀ በመንግሥት በጀት እየተሰሩ ያሉ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተግባራት የሚውሉ አዲስ የተገነቡ ቤቶች እንደገና ሲፈርሱ ታይተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የእግረኛ መንገዶች ተሰርተው፤ ቴራዞ ሁሉ ተነጥፎላቸው ካበቃ በኋላ ዳግም የሚፈርሱበት ሁኔታ ተስተውሏል። የእግረኛ መንገዶቹ ከፈረሱም በኋላ የተነጠፈው ጠጠርና ቴራዞ ዳግሞ ጥቅም በማይሰጥ መልኩ ከተቆፈረ አፈር ጋር የመደባለቅና በአግባቡ ያለማንሳት ችግሮች ይታያሉ። ለአስፓልት ሥራ የሚያገለግል ጠጠር ከፈሰሰና ከተደለደለ በኋላ እንደገና ጠርጎ የማንሳት ችግርም ተስተውሏል።

ወቅቱ የዝናብ ጊዜ ከመሆኑ ጋር ለግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች በዝናብ ተጠርገው እንዳይወሰዱ በአግባቡ ጠብቆ የመያዝ ችግሮችም እየታዩ ነው። በተመሳሳይ የአስፓልት ጠርዞችን በግንባታ ማሽኖች የመሸራረፍም አጋጣሚዎች ይታያሉ። ይህ ደግሞ የተሸራረፉ የመንገድ ጠርዞችን ዳግም ለመስራት ቀላል የማይባል ወጪ የሚጠይቅ ነው።

ስለዚህ ይህ የሕዝብ ሀብት በመሆኑና ሲሚንቶ፣ አሸዋና ጠጠርን የመሰሉ የግንባታ ግብአቶች ዋጋ ጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ የሚመጣ በመሆኑ እነዚህ ግብአቶች ሳይባከኑ በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ግንባታውን የሚያካሂደው አካልም በየቀኑ የግንባታውን ሂደት መከታተልና ሀብት እንዳይባክን የመቆጣጠር ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። ይህ ሲሆን ነው ትክክለኛውን ጊዜ ተጠቅሞ በድፍረት የተገባበትን የኮሪደር ልማት ከውጤት ማድረስ የሚቻለው።

# ዓለም አቀፍ

## ለ239ኛ ጊዜ ለምርጫ የሚወዳደሩት የሕንድ ፖለቲከኛ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፓድ ማራጃን በመባል የሚታወቁት ሕንዳዊ የ65 ዓመት እድሜ ያላቸው አዛውንት ሲሆኑ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ በ238 ምርጫዎች ላይ ተወዳድረዋል።

በተወዳደሩባቸው ሁሉም ምርጫዎች ላይ ሽንፈት ያስተናገዱት እኚህ ፖለቲከኛ "የምርጫ ንጉሥ" የሚል ቅጽል ስምም በሀገሬው ሰው ወጥቶላቸዋል።

በሕንዷ ሜቱር በተሰኘችው ከተማ የሚኖሩት እኚህ ፖለቲከኛ አንድ ቀን በምርጫ አሸንፌ ተመራጭ እሆን ይሆናል ብለው እንደሚያምኑም ተናግረዋል።

ፖለቲከኛው ካደረጓቸው 238 የምርጫ ውድድሮች ውስጥ በፈረንጆቹ 2011 ላይ ያገኙት 6 ሺህ 273 ድምፅ በማምጣት ሁለተኛ የሆኑበት የምርጫ ውጤት በታሪካቸው ከፍተኛው የተባለ ሲሆን በወቅቱ አንደኛ የነበረው ተወዳዳሪ 75 ሺህ ድምጽ አግኝቶ ነበር።


እኚህ ፖለቲከኛ ከሰሞኑ ከሕንድ ብዙኃን መገናኛዎች ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ የምርጫ ውጤትን አሜን ብሎ ለመቀበል ብርታት እንደሚያስፈልግ መናገራቸውን ኦዲቲ ሴንትራል ዘግቧል።

ፖለቲከኛው ለ239ኛ ጊዜም በቅርቡ በሚካሄደው የሕንድ ጠቅላላ ምርጫ ላይ እንደሚወዳደሩ መናገራቸው ትኩረት ስበዋል።

ሽንፈትን አምኖ ለመቀበል ብርታት ያስፈልጋል የሚሉት እኚህ ፖለቲከኛ በቅርቡ በሚካሄደው የሕንድ ምርጫ ላይ ለ239ኛ ጊዜ እንደሚወዳደሩ አስታውቀዋል።

ባለፉት 30 ዓመታት በተካሄዱ ምርጫዎች ላይ ለመመዝገብ በሺዎች የሚቆጠር ገንዘባቸውን ወጪ ማድረጋቸውንም እኚህ ፖለቲከኛ ተናግረዋል።

44 ቀናትን በመፍጀት የዓለማችን ውዱ ምርጫ የሚባለው የሕንድ ምርጫ ከ15 ቀናት በኋላ የሚጀመር ሲሆን 970 ሚሊዮን ዜጎች ድምፅ እንደሚሰጡ ይጠበቃል።



ፓድ ማራጃን



## እስራኤል ወታደሮቿ እረፍት እንዳይጠይቁ አገደች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የእስራኤል ጦር ሁሉም የሀገሪቱ ወታደሮች እረፍት እንዳይጠይቁ ጊዜያዊ ክልከላ አወጣ።

ጦሩ ባወጣው መግለጫ "ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመገምገም ሁሉም በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር እረፍት እንዳይወጣ ተወስኗል፤ እንዳስፈላጊነቱም አዳዲስ ስምሪቶች ሊኖሩ ይችላሉ" ብሏል።

ክልከላው የተላለፈው በምን ምክንያት እንደሆነ ጦሩ በመግለጫው ባያነሳም እስራኤል ከኢራን ጋር የገባችበት ውጥረት ዋነኛው መንስኤ መሆኑን ሬውተርስ ዘግቧል።

ኢራን በሶሪያ ለተገደሉባት ጄኔራሎች የአጸፋ እርምጃ እወስዳለሁ ማለቷን ተከትሎ ቴል አቪቭ የደኅንነት ሥርዓቷን ማጠናከሯ ተገልጿል።

የኢራን ሁለት ጄኔራሎች እና አምስት ወታደራዊ አማካሪዎች በሶሪያ መዲና ደማስቆ በአየር ጥቃት ከተገደሉ በኋላ ቴህራን የአጸፋ እርምጃ እንደምትወስድ መዛቷ ይታወሳል።

እስራኤል እስካሁን ጥቃቱን መፈጸሟን አልገለጸችም፤ የቴህራንን ወቀሳም አላጣጣለችም።

የኢራኑ ፕሬዚዳንት ኢብራሂም ራይሲ ግን ጥቃቱን የፈጸመችው እስራኤል ላይ ፈጣን አጸፋዊ እርምጃ እንወስዳለን ሲሉ መዛታቸው ይታወሳል።

እስራኤል በኢራን ከሚደገፉት የፍልስጤሙ ሀማስ፣ የሊባኖሱ ሄዝቦላህ እና የየመኑ ሃውቲ ጋር ጦርነት ውስጥ ከገባች ከነገ በስቲያ ስድስት ወር ትደፍናለች።

ቴህራን እስካሁን በጋዛው ጦርነት በቀጥታ ባትሳተፍም በምታስታጥቃቸው ኃይሎች ፍላጎቷን እያስፈጸመች መሆኑ ይታመናል።

ባለፈው ሰኞ በደማስቆ ለተፈጸመው ጥቃትም በአጋሮቿ በኩል የአጸፋ እርምጃ ልትወስድ ትችላለ በሚል ቴልአቪቭ የደኅንነት ሥርዓቷን ማጠናከሯ ተገልጿል።

በቴልአቪቭ እና ሌሎች ከተሞች የአቅጣጫ መጠቆሚያ (ጂፒኤስ) አገልግሎት መታወኩን ነዋሪዎች ለሬውተርስ ተናግረዋል። ይህም በጂፒኤስ በሚታዘዙ ሚሳኤሎች የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ ያለመ ነው ተብሏል።

ቴህራን በረመዳን ወር የመጨረሻ ዓርብ ጥቃት ልትፈጽም ትችላለች የሚለው ስጋት ማየሉም እስራኤል ጦሯ በተጠንቀቅ እንዲጠባበቅ እንድታዝ ማድረጉ ተመላክቷል።

የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ባለፈው ወር በጋዛ "አፋጣኝ የተኩስ አቁም እንዲደረግ እና ሁሉም ታጋቾች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እስረኞችን እንዲፈቱ" መጠየቁ የሚታወስ ነው።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
## በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# በመውጫ ፈተና እንደ ሀገር የተከናወኑ ተግባራት

**ጽጌረዳ ጫንያው**

ጥራት ያለው ትምህርት ለስልጣኔ፤ ፍትሐዊ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት፤ ለዜጎች የተደላደለ የስራ እድል ለመፍጠር፤ ሀገርን በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው እንዲሁም በማህበራዊው ዘርፍ ከፍ ለማድረግ ወሳኝ ነው። የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ከሆኑት ተግባራት መካከል ደግሞ አንዱ ፈተና (ምዘና) መሆኑ እሙን ነው። እንደ ሀገርም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ በተለይም የ8ኛ፣ የ12ኛ ከቀድሞ በተሻለ ጥንቃቄ እንዲወስዱ እየተደረገ የመቆየቱ ምስጢር ይኸው ነው።

አሁን የተጀመሩት የዩኒቨርሲቲ መግቢያና መውጫ ፈተናዎችም ይህንን ከማጠናከር አኳያ የማይተካ ሚና አላቸው። በተለይም እንደ ሀገር ትልቁ ስብራት ተደርጎ የተወሰደውን የትምህርት ጥራትና ከደረጃ ወደ ደረጃ የማለፍ ምጣኔን ጉዳይ በእጅጉ ለመፍታት እነዚህ ምዘናዎች ፋዳቸው የጎላ ነው። የዛሬ ትኩረታችን የመውጫ ፈተና ለተማሪዎች ያለውን ፋይዳና እንዴት እንደሚከናወን በስፋት የምናይበት ሲሆን፤ በጉዳይ ላይ በትምህርት ሚኒስቴር የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ ዶክተር ኢዮብ አየነው ማብራሪያ ሰጥተውናል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የመውጫ ፈተና ተማሪዎች በተማሩባቸውና በሰለጠኑባቸው የሙያ ዘርፎች ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል። ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት መያዛቸውን ይለካልም። ከዚህም ባሻገር ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት አሰጣጥ ላይ ያሉበትን ሁኔታ ለማየት ያግዛል። የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅም የጎላ ሚና አለው። የውጤት ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ የሚያስችልም ነው። ስለሆነም መመሪያውን የተከተለ በማድረግም እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ሥራዎች እንዲከናወኑ ተደርገዋል። ተግባራቱን ስንዘረዝር ደግሞ ቅድሚያ የምናደርገው የፈተና ዝግጅቱን ነው።

የመውጫ ፈተና በሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የዝግጅት ሥራ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሲከናወን ቆይቷል። በመውጫ ፈተና ትግበራ በመመሪያው መሰረት የመውጫ ፈተና የሚሰጠው በዓመት ሁለቴ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ፈተና ሐምሌ 2015 ዓ.ም ተሰጥቷል። በዚህም ውጤት ያልመጣላቸውን ተፈታኞችና በ2016 የትምህርት ዘመን አጋማሽ ድረስ ትምህርት የጨረሱ ተማሪዎችን በማካተት በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም ፈተና ለመስጠት ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል። በፈተና ዝግጅቱም በሐምሌ 2015 ዓ.ም ፈተና ወስደው ውጤት ያልመጣለቸውን ተፈታኞች ለዳግም ፈተና መመዝገብ የሚያስቸል ሶፍት ዌር (ፕላት ፎርም) ተዘጋጅቶ ምዝገባቸውን ማከናወን ተችሏል። የአገልግሎት ክፍያቸውን እንዲፈፅሙ ተደርጓል።

የፈተና ዝግጅት ሥራው በዚያ ብቻ ያበቃ እንዳልነበረ የጠቀሱት ዶክተር ኢዮብ፤ የመውጫ ፈተናውን በ2016 ዓ.ም ለመስጠት የሚያስችል ዝርዝር ሁኔታዎችን የያዘ ፕሮፖዛል (የድርጊት መርሀ-ግብር)ን ጨምሮ እንዲዘጋጅ መደረጉን ያስረዳሉ። ይህ ዝግጅት ከትምህርት ፕሮግራሞች እስከ ጥያቄዎች አዘገጃጀት ድረስ የዘለቀ ነውም ብለዋል። በዝግጅቱ 67 የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች የመውጫ ፈተና ጥያቄዎች እንዲዘጋጁ መደረጉንና የአርትኦት ሥራ መስራቱንም ገልጸዋል።

በሁለተኛው ዙር ማለትም በሰኔ ወር 2016 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ለሚሰጠው የመውጫ ፈተና ማስተግበሪያ የድረጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀትና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ተግባራት እንደተከናወኑ የገለጹት ኃላፊው፤ ለዚህም የፈተና ጥያቄ ዝግጅትና የአርትኦት ሥራ የሚካሄድበት ጊዜ ተለይቶ ወደ ሥራ ተገብቷል ይላሉ። የመውጫ ፈተና ተፈታኞች ዝርዝር መረጃ፣ ፈተና የሚሰጥባቸው ፕሮግራሞች፣ ከኢንተርኔት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች፤ የኮምፒዩተሮች ብዛት እና የመሳሰሉትን መረጃዎች የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የማጠናቀርና የመተንተን ስራዎችን መከናወናቸውንም ያነሳሉ።

ሌላው ዶክተር ኢዮብ ያነሱት ጉዳይ በሰኔ ወር 2016 ዓ.ም የመውጫ ፈተናው በሚሰጥባቸው አዲስ 11 የትምህርት መስኮች ላይ ቁልፍ የብቃት መለኪያ እና የፈተና ንድፈ-ማሳያ (Blue Print) ተዘጋጅቶ ለተቋማት ተደራሽ መደረጉን ነው። ተቀራራቢነት ያላቸውን ፕሮግራሞች ከተቋማት በቀረበ ጥያቄ መሰረት የብቃት መኪያና ብሉፕሪንት ሰነዶችን ለማዋሃድ በእቅድ ተይዞ ስምንት ቁልፍ የብቃት መለኪያዎችን የማዋደድ ሥራ መሰራቱን ጠቅሰዋል። ከዚህ በፊት ቁልፍ የብቃት መለኪያ እና የፈተና ንድፈ-ማሳያ (Blue Print) የተዘጋጀላቸው ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ክለሳ የሚያስፈልጋቸው 35 ፕሮግራሞች በመለየት ቁልፍ የብቃት መለኪያና ብሉፕሪንት መከለሱንም አስረድተዋል።

ከመውጫ ፈተናው ጋር በተያያዘ ሌላው የተከናወነው ተግባር የፈተና አሰጣጥና የአስተዳደር ሥራ ሲሆን፤ በዚህ ስር የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የመውጫ ፈተና የሚሰጥባቸው ተቋማት መለየት፣ በተቋማት ያለውን የመውጫ ፈተና ዝግጅት ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በግል እና በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመውጫ ፈተና ለመፈተን የተመዘገቡ ተፈታኞችን በተመረጡ የፈተና ጣቢያዎች መደልደል እና ሞዴል ፈተና መስጠት መሆናቸውንም አመላክተዋል።

በፈተና አሰጣጥ ሂደት የፈተና ጣቢያዎችን በሰባት የፈተና ክላስተር በመለየት በፈተና ጣቢያዎች ለሚገጥሙ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ መስጠት እንደተቻለ ተናግረዋል። ይህ ደግሞ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም እና በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም የተሰጠውን የመውጫ ፈተናን በበይነ መረብ በስኬታማነት ለመስጠት እንዳስቻለም ነው የገለጹት።

የፈተና ውጤት ማሳወቅና ቅሬታ ማስተናገድን በተመለከተ ከተሰሩ ተግባራት አንዱ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም የተከናወነው ሲሆን፤ በ214 የቅድመ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች ለ150ሺህ184 እጩ ተመራቂ ተማሪዎች በኦንላይን የመውጫ ፈተና ተሰጥቷል። በውጤት ሲገለጽም 61ሺህ 054 ማለትም (40.65%) እጩ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተናውን አልፈዋል። ከዚህ ውስጥ 48ሺህ 632 (62.37%) ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሆናቸውም ታውቋል። ከግሎቹ ያለው መጠን 12ሺህ 422 (17.2%) ተማሪዎች እንደሆኑ አስረድተዋል።

በየካቲት 2016 ዓ.ም ደግሞ የመውጫ ፈተናውን የወሰዱት በ215 የቅድመ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች የተመዘገቡት 123ሺህ049 እጩ ተመራቂ ተማሪዎች ሲሆኑ፤ ፈተናውን በኦንላይን ከወሰዱት 97ሺህ673 ተማሪዎች ውስጥ 27ሺህ035 (27.67%) ፈተናውን ማለፍ ችለዋል። ከእነዚህ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈተናውን ከወሰዱት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለፉት 68ነጥብ98 በመቶ እና ከግል ተቋማት ደግሞ 20ነጥብ87 በመቶ ናቸው። በአማካይ ፈተናውን ያለፉት 42ነጥብ03 በመቶ እንደሆኑም ኃላፊው ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪም በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም ፈተናውን ወስደው ያላለፉና በየካቲት 2016 ዓ.ም የመውጫ ፈተና በድጋሚ ከተፈተኑት ውስጥ 32ነትብ80 በመቶ ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና 14ነጥብ89 በመቶ ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሆናቸውን አብራርተዋል። በአማካይ 20ነጥብ89 በመቶ ማለፍ እንደቻሉም አንስተዋል።

በሁለቱም የመውጫ ፈተና የተሰጠባቸው ጊዜያት ከተፈታኞች፣ ከተቋማት እና ከግል ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ማህበር ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን፤ ፈተናው በቴክኖሎጂ ተደግፎ የተሰጠ በመሆኑ የቀረቡት ቅሬታዎች ውጤት የሚያስቀይሩ ባይሆንም ለቀረቡት ቅሬታዎች ተገቢውን መልስ ለመስጠት ኮሚቴ ተቋቁሞ ቅሬታዎች አግባብነት ያለው ውሳኔ እንዲያገኙ መደረጉን ጠቅሰው፤ በሁለቱም የፈተና ወቅቶች የተሰሩ ተግባራትን የሚመለከት፤ የሚገመግም ሪፖርት መዘጋጀቱን አስረድተዋል። ሪፖርቱ መልካም ተሞክሮዎችን እና ተግዳሮቶችን የለየ በመሆኑ ለቀጣይ ሥራ መሻሻል ትልቅ አቅም ይፈጥራልና ይህንን በማጠናከር ዙሪያ ሁሉም ባለድርሻ አካል ርብርብ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

# ስፖርት





# እናትነትና አትሌትነት

ብርሃን ፈይሳ

አትሌቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚደርስባቸው ጉዳት ከተለመደው ልምምድና ውድድር የሚቀርበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ከጉዳታቸው አገግመው ወደቀድሞ ብቃታቸው ለመመለስም ብዙ ፈተናዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሴት አትሌቶች ደግሞ ከዚህ ባለፈ ከውድድር ሊያርቃቸው የሚችል ሌላም ፈተና አለባቸው። ይህም ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከስፖርቱ የሚርቁበት እድል ነው፡፡

ሴት አትሌቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ አስቸጋሪውን ተፈጥሯዊ ሂደት አልፈው ወደ ቀደመ አቋማቸው በመመለስ በውድድሮች ድል መንሳት አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ ነገር ግን በርካታ ብርቱ ሴት አትሌቶችን ያፈራችው ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ወደ ውጤታማነት መመለስ እንደሚቻል በተደጋጋሚ አሳይተው ለሌሎችም ምሳሌ የሆኑባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም፡፡

ከእነዚህ አትሌቶች መካከል አንዷ ደጊቱ አዝመራው ናት፡፡ በረጅም ርቀት ሩጫዎች የምትታወቀው አትሌት ደጊቱ እአአ በ2019 በሞሮኮ በተደረገው የአፍሪካ ጨዋታዎች ላይ በግማሽ ማራቶን ሃገሯን ወክላ በመሳተፍ የብር ሜዳሊያ ባለቤት ነበረች፡፡ በዚያው ዓመት በተደረገው የአምስተርዳም ማራቶን ስታሸንፍ፣ በራክ ግማሽ ማራቶን ደግሞ 4ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው፡፡ በቀጣዩ ዓመት የቫሌንሺያ ማራቶንን በ4ኛነት ስታጠናቅቅ፤ እአአ በ2021 ደግሞ በለንደን ማራቶን 2ኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቋ ይታወሳል፡፡

እመጫቷ አትሌት ደጊቱ ከዚያ በኋላ ያሉትን ጊዜያት በእርግዝና እና ወሊድ ምክንያት ከውድድር መድረኮች ርቃ ቆይታለች፡፡ ከወሊድ መልስ በተያዘው የውድድር ዓመት ግን ወደ ውድድር የተመለሰች ሲሆን፤ ከሳምንታት በፊት በቱኒዚያ በተደረገው የአፍሪካ ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና ሃገሯን ወክላ ተሳትፋለች፡፡ በባርሴሎና ማራቶን ደግሞ አስደናቂ ድልን አስመዝግባለች፡፡

የባርሴሎናውን ውድድር ተከትሎም በርካታ የዓለም መገናኛ ብዙኃን የዘገባ ሽፋናቸውን ያደረጉት የአትሌቷን ጥንካሬ ነበር፡፡ ይህ ጥንካሬ ወደስፔን ከማምራቷ አስቀድሞ ባደረገችው ከፍተኛ ዝግጅት የተገኘ መሆኑን የምታስታውሰው አትሌቷ፤ ከወሊድ በኋላ ጥሩ ሰዓት አስመዝግባ በማሸነፏ ደስተኛ መሆኗን ከአዲስ ዘመን ጋር በነበራት ቆይታ ገልጻለች።

ከእርግዝናዋ ጋር በተያያዘ ከ3 ወር አንስቶ መደበኛ ልምምዷን ብታቆምም ረጅም የእግር መንገድ የመሄድ ልምድ ማዳበሯ ልጇን በምጥ እንድትገላገል ረድቷታል፡፡ ከወሊድ በኋላ ወደ ስፖርቱ ለመመለስ 4 ወር የፈጀባት ሲሆን፤ እስከ 6 ወር እያጠባችም በጂምናዚየም ጥንካሬዋን ልትመልስ ከዚያም ወደ ልምምድ ልትገባ ችላለች፡፡

በባንኮክ ግማሽ ማራቶን ወደ ውድድር በመመለስም 5ኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቅ ችላለች፡፡ በጃንሜዳ ኢንተርናሽናል የሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና ከተወዳደረች በኋላም በታንዛኒያ የነሐስ ሜዳሊያ ለኢትዮጵያ አስገኝታለች፡፡ ከታንዛኒያ መልስ ከሁለት ሳምንት፣ ከወለደች ደግሞ ከ1 ዓመት ከ4 ወር በኋላም ወደ አቋሟ በመመለስ በከባዱ የአትሌቲክስ ውድድር ማራቶን (ባርሴሎና) ከ2ሰዓት ከ20 ደቂቃ በታች በመሮጥ አሸናፊ ልትሆን ችላለች፡፡

ይህንንም ተከትሎ ‹‹ከተሠራ ሁሉም እንደሚቻል ተምሬበታለሁ፡፡ በእርግጥ ሕጻን ልጅን ትቶ ለውድድር ወደሌላ ሃገር መጓዝ ከባድ ነው፤ ነገር ግን ሩጫ ሥራችን በመሆኑ መጠንከር የግድ ነው። አትሌቶች ከወሊድ በኋላ እንደቀድሞ የምንመለስ አይመስለንም ነገር ግን ከልጅ ደስታ በቶሎ ተላቀን ጠንክረን ብንሠራ ወደነበርንበት የማንመለስበት መንገድ የለም፡፡ እኔን መሰል ሴቶች በሕይወታችን ማድረግ ያለብንን በጊዜው ማድረግ አለብን ምክንያቱም ጥንካሬያችን ይመለሳል›› ስትልም መልዕክቷን ታስተላልፋለች፡፡

ደጊቱ ከወሊድ በኋላ በቶሎ ውጤታማ ከመሆኗ ባለፈ ብዙ አትሌቶች የማይደፍሩትን በአጭር ጊዜ ውስጥ ረጃጅም ርቀቶችን በመሮጥ (ሁለት የሃገር አቋራጭ፣ ግማሽ ማራቶን እና ማራቶን) ጥንካሬዋን አስመስክራለች፡፡ ይህም በሥራ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ስጋት ላይ የማይጥልና፤ ራስን ነፃ ማድረግ አስፈላጊ ለመሆኑም ማሳያ ናት፡፡ አትሌቷ አሁን ወደ ቀድሞ አቋሟ የተመለሰች ቢሆንም በምትታወቅበት ማራቶን ግን በበለጠ ጥንካሬና ብቃት ላይ መገኘት እንዳለባት እምነቷ ነው፡፡ በመሆኑም ጠንክራ በመሥራት ለሚቀጥለው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያን ለመወከልም ታልማለች፡፡



ከወሊድ በኋላ አስደናቂ አቋሟን ያሳየችው አትሌት ደጊቱ አዝመራው፤